# አዲስ ዘመን

እፎይ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 003 መስከረም 3 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

# የቀጣዩ ዘመን ተሽከርካሪዎች

**ማርቆስ በላይ**

ከለውጡ ወዲህ መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ላይ ባደረገው የቀረጥ ማበረታቻ በርካታ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር እየገቡ እንደሚገኝ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በርኦ ሀሰን በቅርቡ ለመገናኛ ብዙኃን ገልጸዋል። መንግሥት ያደረገው የቀረጥ ማበረታቻ የባለሀብቱ ተነሳሽነትና የሀገሪቷን የታዳሽ ኃይል አቅርቦት ለማሳደግና የአየር ብክለትን ለመቀነስ እንደሚረዳም ተናግረዋል።

አክለውም፤የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቻርጅ መሙያ ማዕከላት ግንባታን ወደ ክልል ከተሞች የማስፋፋት ሥራና ረጅም ርቀት የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን ወደ ገበያ የማስገባት ሥራ ላይ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል። ለመሆኑ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ልማት ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎችና የሚኖራቸው ሀገራዊ ጠቀሜታ ምን ይሆን?

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ


**የቀጣዩ ዘመን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**




# ግብርናን እያሻገረ ያለው የግብዓት አቅርቦት

**ታደሠ ብናልፈው**

**ዜና ትንታኔ**

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፤ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ዘርፉን የማዘመንና በቴክኖሎጂ የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው።

ግብርናው ከድህነት ቅርቃር፣ ከኋላ ቀርነት አሠራር ወጥቶ የሀገርን ኢኮኖሚ እንዲገነባ የአፈር ማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘር፣ የኮምባይነር፤ የትራክተርና መሰል ግብዓቶችን የማቅረብ ሥራ


**ግብርናን እያሻገረ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**


# ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ከቅርብ ርቀት

**ሄለን ወንድምነው**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ቀርፃና አፅድቃ ወደ ሥራ ከገባች ሰነባብታለች። ዲጂታል ኢትዮጵያ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ዕድሎችን በመጠቀም ፈጠራ የታከለበትና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል በኢትዮጵያ መንግሥት የሚመራ ተነሳሽነት ነው።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ ሽግግር በአካል ከሚደረጉ ግንኙነቶች ወጥቶ የዲጂታል አሠራሮችን በመተግበር ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመድረስ የሚደረግ ጥረት ነው። የዲጂታል የሽግግር መንግሥት፣ በንግድ ድርጅቶች እና በማህበረሰቡ መካከል በአካል የሚያደርጉትን ግንኙነት በበይነ መረብ የመቀየር ሥራ ነው።

የኢትዮጵያ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን በግንባር ቀደምትነት ለመምራት የሚችሉና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሊጠቀሙ የሚችሉ አራት ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ዘርፎችን ለይቷል። የተለዩት ዘርፎችም ግብርና፣ የማምረቻ ዘርፍ፣ የመረጃ ቴክኖሎጂና ቱሪዝም ናቸው።

የዲጂታል ቴክኖሎጂ አቅምና አጠቃቀምን በሚፈለገው ደረጃ ማሳደግ ለሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያበረክተውን




አስተዋጽኦ በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ ዶክተር አብዮት ባዩ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት የዲጂታል ክህሎትና እውቀት ለሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ነው። በጤና፣ በትምህርት፣ በግብርና እና በማንኛውም መስክ የሚሰሩ ሥራዎች የዲጂታል ክህሎትን ይፈልጋሉ። የመግባቢያ፣ የመገልገያ እና የማምረቻ መሳሪያዎችም በዲጂታል ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

በዚህም ማንኛውም ሰው ሥራውን ለማከናወን የዲጂታል ክህሎት ያስፈልገዋል። የዲጂታል እውቀትና ክህሎት በሌለበት ሁኔታ የሀገርን ኢኮኖሚ ሊደግፍ የሚችል የሰው ኃይል ማፍራት ከባድ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ በዲጂታል ክህሎት ወደኋላ ቀርታለች የሚሉት ዶክተር አብዮት፤የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ሀገራትም አንጻር ወደኋላ ቀርታለች ብሎ ያስቀምጣል። ኢትዮጵያን በዲጂታል ክህሎት ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ለማድረግ በርከት ያሉ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ክህሎት ስልጠና ቀርጾ መተግበር እንደሚገባ ስትራቴጂውን ዋቢ አድርገው ይገልጻሉ።


አሁን ላይ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ቀርጻ ወደ ተግባር መግባቷና አምስት ሚሊዮን ወጣቶችን በዲጂታል ማሰልጠን መጀመሯ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ ወሳኝ ነው። ከኢኮኖሚ ግንባታ ባለፈም በርከት ያሉ ወጣቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ በማሰልጠን በቴክኖሎጂ ካደጉ ሀገራት ተርታ እንድትሰለፍ እድል ይፈጥራል ይላሉ።

በቀጣይም የዲጂታል ክህሎት ያላቸው ዜጎችን ለማፍራትና የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማትን ለማስፋፋት ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ በአጽንኦት ያስረዳሉ።


**ዲጂታል ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል**



ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565


መምህርት ዲቦራ ስንታየሁ

# ችግር ያዋለደው የአጥንት ኢንፌክሽን መመርመሪያ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ሐተታ**

ችግር ብልሃትን ትወልዳለች። ችግርን ማወቅ በራሱ ለችግሩ የመፍትሔው ግማሽ አካል ነው የሚባለውም ለዚሁ ይመስላል። አብዛኞቹ የፈጠራ ሥራዎች መነሻቸው ችግር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ብዙ የዓለማችን የየዘርፉ ሊሂቃንም ከአካባቢያቸው ችግር አልያም ከማህበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸው በመነሳት የተለያዩ ዓለም አቀፍ እፎይታን የሚፈጥሩ ሥራዎች አበርክተዋል።

ታዲያ በኢትዮጵያም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢኖቬሽንና ፈጠራ እንዲሁም በንግድ ፈጠራ ሃሳብ ዘርፍ በርካታ ወጣቶች እየተሳተፉ ይገኛሉ። በተለይ እንደ ሀገር በተጀመሩት ስታርታፕ እና ብሩህ የንግድ ፈጠራ ሃሳብ ውድድር የተለያዩ ችግር ፈቺ የቴክኖሎጂና የንግድ ሃሳቦች እየፈለቁ ይገኛል።

በዚህም ወጣቶች በገፍ እየተሳተፉ ነው። በቅርቡም በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አዘጋጅነት ለሁለት ሳምንታት ሲካሄድ የቆየው ብሩህ የንግድ ፈጠራ ሃሳብ ውድድር ማጠቃለያ ተካሂዶ 125 ተወዳዳሪዎች በሠሯቸው የቴክኖሎጂና የንግድ ፈጠራ ሃሳቦች የሁለት ሺህ ዶላር ተሸላሚ ሆነዋል። ከእነዚህም መካከል የአጥንት ኢንፌክሽን መመርመሪያ ማሽን መፍጠር የቻለችው ዲቦራ ስንታየሁ አንዷ ናት።

ዲቦራ ስንታየሁ ትባላለች። ትውልድና እድገቷ ወላይታ ሶዶ ከተማ ሲሆን፤ በወላይታ ዩኒቨርሲቲ መምህርትም ናት። የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪዋን በባዮ ሜዲካል ምህንድስና ጅማ ዩኒቨርሲቲ ተከታትላለች። በተጨማሪም በሳንፎርድ ዩኒቨርሲቲ በሰው ሰራሽ አስተውሎት ሰርተፊኬት አግኝታለች። በ15 ደቂቃ ውስጥ ያለምንም ቀዶ ጥገና የአጥንት ኢንፌክሽን መለየት የሚችል ማሽን መፍጠር ችላለች። ፈጠራውን ለመስራት የተለያዩ ጥናቶች ከቡድን አጋሮቿ ጋር መመልከት እንደቻለችም ትገልጻለች።

ከሦስት ዓመት በፊት በደረሰባት የመኪና አደጋ የአጥንት መሰበር አጋጥሟት ብረት እግሯ ውስጥ ቢገባም እግሯ ሳይድን ብረቱ በመሰበሩ ለከፍተኛ የአጥንት ኢንፌክሽን ችግር በመጋለጧ ፈጠራውን ለመሥራት ይበልጥ እንዳነሳሳት ለኢፕድ ቃሏን በሰጠችበት ወቅት ተናግራለች።

በዚያን ጊዜ መመርመሪያ ማሽኑ በቅርብ ባለመኖሩ ለከፍተኛ ህመም መዳረጓ ብቻ ሳይሆን ናሙና ተወስዶ የምርመራውን ውጤት ለማወቅ ከሦስት ሳምንት በላይ ወስዶ እንደነበር የምታስታውሰው መምህር ዲቦራ፤ በአደጋው ምክንያት የአጥንቴ መሰበር በ15 ደቂቃ ውስጥ የአጥንት ኢንፌክሽን መመርመር የሚችል ማሽን እንድፈጥር አግዞኛል ትላለች።

ማሽኑ በተጨማሪም ለተለያዩ ቴራፒዎች፣ ለጡት ካንሰር እና ለዲስክ ህክምናም የሚያገለግል ስለመሆኑንም ታስረዳለች። የአጥንት ኢንፌክሽኑ በወቅቱ ባለመታወቁ ለከፍተኛ ህመምና ለተጨማሪ በሽታ ዳርጓት እንደነበርም ትናገራለች።

እንደ መምህር ዲቦራ ገለጻ፤ መመርመሪያው ምንም አይነት ጨረር አለመጠቀሙ፣ ገበያ ላይ ከሚገኙ ኤክስሬይ ማሽኖች በተሻለ ሁኔታ አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑ፣ የተለያዩ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ፊውቸሮች(ሶፍት ዌሮች) የያዘ መሆኑ፣የማሽኑ መስሪያ ግብዓቶች ከ95 በመቶ በላይ በሀገር ውስጥ የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረቡ ለየት ያደርገዋል።

ችግሩ የኔ ብቻ ሳይሆን ከሰሃራ በታች ባሉ ሀገሮች ከ54 በመቶ በላይ የሚሆኑ ወጣቶች በዚህ ችግር እንደሚሰቃዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ የምትለው መምህርቷ፤ ይህም በወጣቱ ላይ ከፍተኛ አእምሯዊና አካላዊ ጫና ከማሳደሩም በላይ ህይወት እስከ ማሳጣት የሚያደርስ እንደሆነ ታብራራለች።

መምህር ዲቦራ ማሽኑን ለመውሰድ የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ተቋማት ፍላጎት እንዳላቸው ገልጸውልናል ያለች ሲሆን፤ በጅማና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ሙከራ ተደርጎ ጥሩ የሆነ ምላሽ እንዳለ ታክላለች።

አንዱ ማሽን በሁለት መቶ ሺህ ብር እየቀረበ መሆኑን ጠቅሳ፤ በቀጣይም የተለያዩ ማሻሻያዎች በመጨመር ለብዙ በሽታዎች እንዲሆን ለማድረግ ታቅዷልም ባይ ናት። በተጨማሪም በብዛት ለማምረት ብዙ አቅም የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ ፈንዶች እያፈላለች እንደምትገኝም ጠቁማለች።

# ቡና - ከኢኮኖሚ ባሻገር ያለው ማህበራዊ ፋይዳ

**አዲሱ ገረመው**

ሥፍራው አረንጓዴ ኩታውን ተከናንቧል። የኮረብታዎች እና የሸለቆዎች ልምላሜ የጠቢብ ቄንጠኛ የቀለም ቅብ ውጤቶች መስለው ተሰትረዋል። ተሻግሮ የሚታየው ጥቅጥቅ ያለው የክረምት ደመና መሬቱን ከሰማይ ጋር የተዋሃደ አስመስሎታል።

የወሎ ጭስ፣ ጨሶ ጨሶ ሀገር ምድሩን የሞላው መስሏል። ወሎ ጭሱ ሲታሰብ ቡናው፣ ቡናው ሲታሰብ ሥርዓቱ፣ ሥርዓቱ ሲታሰብ ባህሉ ተሰናስሎ እንደ ሃብል የሚመዘዝበት ሥፍራ ነው።

በተለይ በወሎ እምብርት ደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ ውስጥ ቡና ከመጠጥ በላይ ነው። ቡና በወሎ ባህል፣ በረከት እና ትስስር ነው። የወሎ ሕዝብ የቡና ሥነ ሥርዓቱ እንደ ልዩ የአብሮነት ዕሴት ይዞት የቆየ ሲሆን፤ ይህም የሰላም፣ የጤና እና የብልጽግና ምርቃት በአዲስ የተፈላ ቡና መዓዛ ሲሸፈን ያሳያል።

የጉዟችን መዳረሻ በሆነው በዚህ ስፍራ የቡና ትሩፋት ዘርፈ ብዙ ነው። ሥነሥርዓቱና ባህሉ ለትውልዶች ተላልፏል። "ቡና ከመጠጥ በላይ የአንድነት ምልክት መሆኑን ታላላቆቻችን አስተምረውናል፤ እኛም የእነርሱን አርዓያ ተከትለን ባህሉን ጠብቀን እዚህ አድርሰነዋል።" ሲሉ የደቡብ ወሎ ወረባቦ ወረዳ ነዋሪዋ ወይዘሮ ካድራ እሸቱ ይናገራሉ።


ወይዘሮ ካድራ እንደሚሉት፤ በዚህ ስፍራ ቡና ሲፈላ ሲል ጽዱ ቦታ ይዘጋጃል። ይህ ደግሞ የቡና ሥርዓት ድባቡ ለበረከትና ለጸሎት እንዲውል ጭምር በማሰብ የሚከወን ነው።

ወይዘሮ ካድራ እንደ ብዙ የወሎ ሴቶች ሁሉ ቡናን እንደ ሰላም፣ አንድነት፣ አብሮነትና በረከት ድልድይ ነው የሚያዩት። ምክንያቱም ደግሞ የቡና ሥርዓቱ የአማራ፣ የኦሮሞ ወይም የትግራይ፣ የሙስሊምም ይሁን የክርስቲያን ሕዝቦችን የሚያገናኝ ነው ይላሉ።

"ወሎ ውስጥ ብዙ ማንነቶች አሉን፤ ነገር ግን ቡና ስንጠጣ አንድ ሰው ነን" ሲሉ በኩራት በተሞላ ድምጽ ይናገራሉ። የወሎ የቡና ሥነ ሥርዓቱ ሀገርን ቤተሰብን፣ ልጆችን፣ አጠቃላይ የወደ ፊት ህይወትን የሚመርቁበት ስለመሆኑ ነው የሚጠቅሱት።

በቅርቡ የደቡብ ወሎ ዞን ሕዝብ ይህንን ለዘመናት የቆየ ባህል ለማስቀጠልና ማህበረሰቡን ለማጠናከር የሚያስችል አዲስ ጉዞ ጀምሯል።

በክልሉ እየተካሄደ ያለውን የችግኝ ተከላ ፕሮጀክት ለመዘገብ በሄድንበት ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ የቡና ችግኞችን ተከላ ተመልክተናል። እናቶችና ሴት ልጆች እንደዛሬው ሁሉ በቡና ሥርዓቱ ልዩ ምርቃት የነገውንም


ወይዘሮ አይሻ ኢብራሂም


ወይዘሮ ካድራ እሸቱ


ወይዘሮ እናኒ ሽፈራው

የደስታ ዘር ለመዝራት ተሰብስበው የቡና ችግኝ ተክለዋል።ሌላኛዋ እናት ወይዘሮ እናኒ ሽፈራው፤ ብዙ ቤተሰቦች እንዳላቸው፤ ቤተሰቦቻቸውን ጨምሮ ከጎረቤት ጋር ተጠራርተው ቡና እንደሚጠጡና የቡና ድባቡም ልዩ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ቡና ከጊዜ ወደ ጊዜ ዋጋው እየጨመረ መምጣቱ ባህሉን እንዳያደበዝዘው ስጋት ፈጥሮባቸው እንደነበርና አሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚከናወነው የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ ምክንያት የቡና ተከላ መስፋፋቱ ተስፋቸውን ዳግም የጠገነው ስለመሆኑም ይናገራሉ።

የቡና ተክሉ እርሳቸው ነዋሪ በሆኑበት ደቡብ ወሎ ዞን በስፋት እየተተከለ መሆኑን ጠቅሰው፤ “በጥቂት ዓመታት ውስጥ የራሳችንን ቡና ማምረት የምንችለው ለቤተሰባችን ብቻ ሳይሆን ለገበያ ለመሸጥ ጭምር ነው” ብለዋል። ይህ ደግሞ የአካባቢውን የቡና ሥርዓት ባህሉን ጠብቆ እንዲቆይ ብሎም የአብሮነት መንፈስን ለሌላው ለማጋራት አስቻይ ነው ብለዋል።

ወይዘሮ እናኒ የቡና ዛፎችን መትከል ከግብርና ተነሳሽነት ባለፈ ባህሉን መልሶ ለማግኘት እና ህልውናውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መንገድ ነው ሲሉ ገልጸዋል። "ይህ ገንዘብ ከማግኘት የበለጠ ነገር ነው። ባህላችንን መጠበቅ እና ለልጆቻችን ለማስተላለፍ ይረዳል" በማለትም ነው የተናገሩት።

ቡና በወሎ ያለው ፋይዳ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ያለፈ ነው። ከማህበረሰቡ የአንድነት ስሜት እና ከሰላም ምኞቱ ጋር በጥልቅ የተሳሰረ መሆኑን ወይዘሮ እናኒ ይጠቅሳሉ። "ቡና ስንጠራራ ለመጠጣት ብቻ ሳይሆን ሰላም እየፈጠርን ነው" በማለት በእያንዳንዱ የቡና ሥርዓት ውስጥ ለጎረቤት፣ ለልጆች እና ሀገር ጸሎት መኖሩን አውስተዋል።

ይህ የምርቃት በረከትም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይድረስ እርፎ መረባ፣ ሀገር አማን ይሁን፣ ልጆች ይደጉልን፣ መንግሥት ይጽናልን፣ የምንዘራውና የምንተክለው ለዘር ይብቃ በሚሉ የመልካም ምኞት ገላጭ ቃላት መመራረቅ የተለመደ ነው ብለዋል።

የቡና ሥነ-ሥርዓት የአስተሳሰብና የአንድነት ጊዜ መሆኑን የሚናገሩት ደግሞ በደቡብ ወሎ ዞን ወረባቦ ወረዳ 01 ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ አይሻ ኢብራሂም ናቸው። "በወሎ ውስጥ ያለን ልዩነት ቢኖርም ለአብሮነት ሁሌም ዋጋ እንሰጣለን። ቡና አንድ ያደርገናል፤ በዚህም ለወደፊት ሰላም ያለንን ተስፋ እንጋራለን" ሲሉ ገልጸዋል።

የቡና ችግኝ እያደገ በሄደ ቁጥር በወሎ ሕዝብ መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያ እንድትሆን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያበረክቱ ወይዘሮ አይሻ ገልጸዋል። ቡና ካለው ባህላዊ ፋይዳ አንጻር ችግኙን በመትከል ረገድ ሴቶች ያሳዩት ቁርጠኝነትና ጽናት ከምንም በላይ አንድነትን የሚያከብር ማህበረሰብ ጥንካሬን ያሳያል ነው ያሉት።

በወሎ ሴቶች ቡና በመትከል የተስፋ፣ የሰላምና የብልጽግና ዘር እየዘሩ ነው ያሉት ወይዘሮ አይሻ፤ በመጪው ጊዜ ባህሉ ተጠናክሮ ለሀገር አንድነትና ሰላም ተምሳሌት ይሆን ዘንድም ተመኝተዋል።

"አንድ ቀን ልጆቻችን ቡና ሊጠጡ ሲቀመጡ እናቶቻቸው እና አያቶቻቸው በተባረኩ እጆቻቸው እነዚህን ዛፎች እንደተከሉ ያስታውሳሉ" በማለት፤ ይህም ለእነርሱና ለኢትዮጵያ ሰላም የተከፈለ ዋጋ ስለመሆኑም ያውቃሉ ነው ያሉት።

የወሎ የቡና ሥነ ሥርዓት ታሪክ መጠጥ ብቻ አይደለም። የፅናት፣ የአንድነት እና የተስፋ ታሪክ ነው። ማህበረሰቡ በቡና ሥነ ሥርዓቱ እየተካፈለ፣ እያንዳንዱ ጸሎት ሲያደርግ ሀገሩን እያሰበ በመሆኑ ይህ የቡና ዘር በወሎ የበለፀገ አፈር ላይ መብቀሉ የሕዝቡን የአንድነት ታሪኩን ይበልጥ የሚያጎለብት መሆኑን እናቶች ገልጸዋል።

# የፍትህ ዘርፍን የሪፎርም ሥራዎች ሊደግፍ የሚችል የለውጥ ፍኖተ ካርታ ተዘጋጀ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ የሚገኙትን የፍትህ ዘርፍ የሪፎርም ሥራዎች ሊደግፍ የሚችል እና ለሦስት ዓመታት ተግባራዊ የሚሆን የሕግ እና ፍትህ ዘርፍ የለውጥ ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱን የፌዴራል የፍትሕና ሕግ ኢንስቲትዩት ገለጸ።

ኢንስቲትዩቱ ከፌዴራል የፍትህ አካላት እና የክልል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩቶች ጋር የ2016 ዓ.ም እቅድ አፈጻጸም እና በ2017 ዓ.ም እቅድ ዙሪያ ውይይት አካሂዷል።

ዋና ዳይሬክተሩ አምባሳደር ደግፌ ቡላ እንደገለጹት፤ ፍኖተ ካርታው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተካሄዱ የሚገኙትን የሕግና ፍትህ ሪፎርም ሥራዎች ሊደግፉ የሚችሉና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠትን ማዕከል ያደረጉ ናቸው።

ከ2017ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት ተግባራዊ በሚደረገው መርሀ ግብር፤ ክልሎችም ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር የተናበበ የራሳቸው ፍኖተ ካርታ አዘጋጅተው ከፌዴራል ጋር በመናበብ ይተገብራሉ ብለዋል።

በቀጣይ ትግበራ በዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመገልገል ያደጉ ሀገራት የሚጠቀሙበትን የተለመደ አሠራር በመጠቀም የዘርፉ ባለሙያዎች በቨርቹዋል ስልጠና እንዲወስዱ እንደሚደረግም አምባሳደር ደግፌ ገልጸዋል።

ትግበራው የተገልጋዮችን እንግልት በማስቀረት እና ወጪ በመቀነስ ተገልጋዮች ፈጣን ፍትህ እንዲያገኙ በማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትም አመልክተዋል።


አምባሳደር ደግፌ ቡላ

ፍኖተ ካርታው የፍትህ ተደራሽነትን በማሳደግም ባለጉዳዮች ባሉበት ቦታ ሆነው የሚዳኙበትና ፍርድ የሚያገኙበትን ሥርዓት መዘርጋት ማካተቱንም ጠቁመዋል።

የጥናትና ምርምር ሥራዎች በተመረጡ እና ሀገራዊ ለውጡን በሚያሳኩ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲከወኑ በማድረግ ለሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ግብአት እንዲሆኑ እንደሚሠራም አመልክተዋል።

የሕግና የፍትህ ተቋማት ትኩረት የሚያደርጉት እና በአዋጅም የተሰጣቸው ስልጣንና ኃላፊነት ለዳኞች፣ ለዐቃቤ ህጎች፣ ለማረሚያ ቤቶችና ለፖሊሶች ስልጠና መስጠት እና ጥናትና ምርምር ማካሄድ መሆኑን ጠቁመው፤ በፍኖተ ካርታውም እነዚህ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸው መካተታቸውን ጠቁመዋል።

የዳኞችን አቅም ለማጎልበት በዕውቀት እና በሥነ ምግባር ዙሪያ ስልጠና ይሰጣቸዋል፤ በሥራ ሂደት የሚያስቸግሯቸውን ጉዳዮች በመለየት ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል። ለዐቃቤ ሕጎችም በተመሳሳይ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል ሲሉም አክለዋል።

የምርመራ ሥራ ዘመኑን የሚመጥን መሆን እንዳለበት በመጠቆምም፤ ለመርማሪ ፖሊሶች ከምርመራ ሥራ ጋር የተያያዘ ሳይንሳዊ መንገድን የተከተለ፣ የወንጀል ምርመራ ታክቲክና ቴክኒክን በለየ መልኩ ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግበት ሥርዓት በፍኖተ ካርታው መካተቱንም አመልክተዋል።

የሰው ኃይል፣ የቴክኖሎጂ እና የስልጠና አካሄዶችና ስልቶች መካተታቸውንም አምባሳደር ደግፌ ተናግረዋል።

ኢንስቲትዩቱ በተለይም ከሕግና ፍትህ ጥናት እና ምርምር ሥራ አንጻር የባለሙያ እጥረት፣ የምርምር ክህሎት ማነስ፣ ለምርምር ሥራ የሚያስፈልጉ መረጃዎች እጥረት፣ የኢንስቲትዩቱ የምርምር ፖሊሲ አለመኖር እና የጥናት ውጤቶች በተሟላ ሁኔታ አለመተግበር ተልዕኮውን ለመፈፀም በሚያደርገው ጥረት እንቅፋት እንደሆኑበት ተጠቅሷል።

ለሥራ ክፍሎች የሰው ኃይል የማሟላት፣ ግብአቶችን በወቅቱና በአግባቡ ማቅረብ፣ ሳቢ ጥቅማ ጥቅም ማሟላት እንዲሁም በሚታዩ ችግሮችና ክፍተቶች ወቅታዊ እርምት መስጠት ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸው ተጠቁሟል።

# የተመጣጠነ አመጋገብ ለጤና

**ታደሠ ብናልፈው**

የኢትዮጵያ የአመጋገብ ባህል የተወሰኑ የምግብ አይነቶች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሕፃናት መቀንጨር፤ መቀጨጭ እያጋጠመ ነው፤ በመቀንጨር ምክንያትም ሀገሪቱ በዓመት 55 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር እያጣች ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ይፋ ባደረገው የአመጋገብ ሥርዓት በአንድ የምግብ ማዕድ ላይ አራት የምግብ ምድብ መገኘት አለበት፤ ሳይንሱ የሰው ልጅ በቀን ስድስት የምግብ ምድቦችን በመጠኑ መመገብ አለበት ቢልም በኢትዮጵያ በኢኮኖሚና በግንዛቤ እጥረት ምክንያት ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ እየተመገቡ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡

የተመጣጠነ ምግብ ዜጎች አለመመገባቸው፤ ሕፃናትን ለቅንጨራና ለቅጨጫ ሲያጋልጥ 67 በመቶ የሚሆነው አምራች ኃይል ደግሞ በአካልና በአዕምሮ የቀነጨረ እንዲሆን ማድረጉን አመላክቷል፤ የመቀንጨሩ ማሳያም የትምህርት አቀባበሉ ዝቀተኛ፤ ቴክኖሎጂን የመላመድ ባህሉ አነስተኛና በክስተቶች ምክንያታዊ ያልሆነ መሆኑ ማሳያ ነው፡፡

መጋቢት14 ቀን 2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትና የጤና ሚኒስቴር ከተባባሪ አካላት ጋር ባከናወኑት የምግብና ሥርዓተ ምግብ ስትራቴጂ መነሻ ዳሰሳ ጥናት፣ በሁሉም ክልሎች ዝቅተኛ የምርት ስብጥር በመኖሩ ሕፃናት የመቀንጨር ምጣኔ እ.ኤ.አ. በ2016 ዓ.ም ድረስ ከነበረው ብዙም ለውጥ አላሳየም ይላል፡፡

ባልተስተካከለ የአመጋገብ ሥርዓት ምክንያት ከአምስት ዓመት በታች ከሚገኙ ሕፃናት ውስጥ 39 በመቶው መቀንጨር አጋጥሟቸዋል፤ 11 በመቶ የሚሆኑት ካላቸው ቁመት ጋር የሚመጣጠን ክብደት የላቸውም፤ 22 በመቶ የሚሆኑት በዕድሜያቸው ሊኖራቸው የሚገባ ክብደት እንደሌላቸው በጥናቱ ተቀምጧል፡፡

ስድስት በመቶ የሚሆኑ ሕፃናት ሰውነት ከሚያስፈልገው በላይ ምግብ በመመገብ በዕድሜያቸው ሊኖራቸው ከሚገባ ክብደት በላይ ማስመዝገባቸውንም በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

በሁሉም ክልሎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ለአካለ መጠን የደረሱ ሴቶች፣ በወጣትነትና በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶችና ሕፃናት የንጥረ ምግቦች እጥረት ተጎጂ ናቸው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከአምስት ዓመት በታች ከሚገኙ ሕፃናት ግማሽ ያህሉ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት የተጎዱ ሲሆኑ፤ ከተጎዱትም ውስጥ 43 በመቶ የሚሆኑት በገጠር፤ 29 በመቶ የሚሆኑት በከተማ ይገኛሉ፡፡

በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች የተመጣጠነ ምግብ ያለማግኘት ምጣኔ የተለያየ ነው፤ የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘት የመቀንጨር መጠን በአፋር 42 በመቶ፣ በኦሮሚያ 41 በመቶ፣ በአማራ 40 በመቶ፣ በደቡብ 40 በመቶ መሆኑን በጥናቱ ተዳሷል፡፡

በሀገሪቱ ለአቅመ አዳም ከደረሱ ሴቶች ውስጥ 19 በመቶ




የሚሆኑት መመዘን የሚገባቸው ከክብደት በታች ናቸው። ከክብደት በታች ከሆኑ 19 በመቶ ውስጥ 22 በመቶ የሚሆኑት በገጠር፣ 15 በመቶ የሚሆኑት በከተማ የሚኖሩ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ከስድስት እስከ 23 ወራት ከሚገኙ ሕፃናት ውስጥ 47 በመቶ የሚሆኑት ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያጋጠማቸው ሲሆኑ፤ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ካጋጠማቸው 47 በመቶ ውስጥ 75 በመቶ በሶማሌ፣ 53 በመቶ በደቡብ፣ 50 በመቶ በጋምቤላ የሚገኙ ናቸው፡፡ 45 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ መካከለኛ የምግብ እጥረት አለባቸው፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ነሐሴ 9/2016 ዓ.ም የሰቆጣን ቃል ኪዳን ስምምነትና የማስፋፊያ ምዕራፍ ስትራቴጂ ትግበራና የቀጣይ እቅዶችን በተመለከተ በተካሄደው ውይይት ላይ እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ ከሁለት ዓመት በታች የሚገኙ ሁለት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሕፃናት መቀንጨር ላይ ይገኛሉ፡፡

በተመሳሳይ ቀን የጤና ሚኒስትር ዶክተር መቅደስ ዳባ፤ በኢትዮጵያ ከአምስት ዓመት በታች የቀነጨሩ 39 በመቶ፤ የቀጨጩ 11 በመቶ ሕፃናት አሉ፡፡

በጤና ሚኒስቴር የሥርዓተ ምግብ ባለሙያ ወይዘሮ ቤዛዊት ወርቁ በሰጡት አስተያየት፤የኢትዮጵያ ማህበረሰብ የአመጋገብ ሥርዓት ኃይልና ሙቀት ሰጪ እንዲሁም ጣፋጭ ምግቦች ላይ ያተኮረ ነው፤ይህም የአመጋገብ ሥርዓት ለአላስፈላጊ ውፍረት እየዳረገ ነው፡፡

በከተማ ማህበረሰብ ዘንድ ጣፋጭ፣ ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦችን ሕፃናት እየተመገቡ ለአላስፈላጊ ውፍረት እየተጋለጡ ነው ብለዋል፡፡

ማህበረሰቡ የተመጣጠነ ምግብ ማለትም ኃይልና ሙቀት ሰጪ፤ ገንቢ፤ በሽታ ተከላካይ፣ ቅባትና ማዕድናት የያዘ የአመጋገብ ሥርዓት የለውም፤ በተለይ አትክልትና ፍራፍሬን የመጠቀም ባህሉ ዝቀተኛ ነው ሲሉ ይናገራሉ፡፡

ሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ ባለማግኘታቸው ለቅንጨራና ለቀጫጫነት እየተጋለጡ ነው፤ የሕፃናትን መቀንጨርና መቀጨጭን ለመከላከል የተመጣጠነ ምግብ አልባ የሆነውን የአመጋገብ ሥርዓትን ማስወገድ ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ ሥርዓትን ማዳበር የተስተካከለ ጤና፤ አቋም፤ ፈጣን የትምህርት አቀባበልና የቴክኖሎጂ አቀባበል፤ በቀላሉ ለበሽታ የማይጋለጥና ቢጠቃም በህክምና ቶሎ የሚያገግም አካል እንዲኖር ያደርጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የሥርዓተ ምግብ ባለሙያ ቢራራ መለሰ በበኩላቸው፤ የሀገሪቱ የአመጋገብ ባህል የተወሰኑ ምግቦች ላይ የተዛመደ ነው፤ አትክልትና ፍራፍሬን የመጠቀም ባህል ዝቅተኛ ነው፡፡

በአንድ የምግብ ማዕድ አራት የምግብ ምድቦች፤ በቀን ስድስት የምግብ አይነቶች አስፈላጊ ናቸው፤ዜጎች ግን በኢኮኖሚና በግንዛቤ እጥረት የተመጣጠነ ምግብ እየተመገቡ አይደለም፤ ባለመመገብም የአካልና የአዕምሮ መቀንጨር ምክንያታዊ አልባ ትውልድ እየተፈጠረ ነው ይላሉ፡፡

አንድ ሰው በቀን ስድስት የምግብ ምድቦችን ማለትም የኃይልና ሙቀት ሰጪ፤ በሽታ ተከላካይ፣ ገንቢ፣ ማዕድን፣ ቅባት ምግቦችን በመጠኑ ማግኘት አለበት ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

እአአ አቆጣጠር በ2023 ዓ.ም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባደረገው ጥናት፤ በሀገሪቱ እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ 39 በመቶ የሚሆኑት የቀነጨሩ፤ 22 በመቶዎች እድገታቸው ከሚጠበቀው በታች፤ 11 በመቶ የአጭር ጊዜ የምግብ እጥረት ያጋጠማቸው ናቸው፤ ስድስት በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የምግብ አቅርቦት አግኝተው ከልክ በላይ በመመገብ ለአላስፈላጊ ውፍረትና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የተጋለጡ ናቸው ሲሉ ተናግረዋል፡፡ በኢትዮጵያ ዜጎች የተመጣጠነ ምግብ ባለመመገባቸው 67 በመቶ የሆነውን አምራች ወጣት በአካልና በአዕምሮ እንዲቀነጭር አድርጎታል፤ ትምህርትን በፍጥነት የሚቀበል፤ ፈጠራን አስፋፍቶ ችግር የሚፈታ፤ ቴክኖሎጂን በቶሎ የሚላመድና በክስተቶችና በነገሮች ምክንያታዊ የሆነ ወጣት ለማፍራት አመጋገብ ሥርዓትን ማመጣጠን እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡

ሀገሪቱ የአመጋገብ ሥርዓት አለመስተካከል በሚደርስ መቀንጨር ምክንያት 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ታጣለች፤ በመቀንጨር ምክንያት የምታጣውን 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለማዳን፤ አምራች ዜጋዋን ሙሉ አቅም ተጠቅማ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ ባህልን ማዳበር ተገቢ ነው ሲሉ ይናገራሉ፡፡

የተመጣጠነ የምግብ ሥርዓት የተስተካከለ አቋም፣ ጤናማ አካል፣ በሽታን የሚከላከልና ከበሽታ ቶሎ የሚያገግም፤ ትምህርትን፤ ቴክኖሎጂን በፍጥነት የሚቀበልና የሚላመድ፣ የፈጠራ ሥራ የሚሠራ፤ ሀገርንና ሕዝብን በሥነ ምግባር የሚያስተዳድር ዜጋ ለመፍጠር ትልቅ ጠቀሜታ አለው ብለዋል፡፡

የተመጣጠነ ምግብ ብቻውን አካላዊ፣ አዕምሮዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ማምጣት አይችልም፤ አካላዊ እንቅስቃሴ መስራት ተገቢ ነው ሲሉም ጠቁመዋል፡፡



አቶ በላይ ደጀን

# ለነገ ጤነኛና ብቁ ሀገር ተረካቢዎችን ለማፍራት ዛሬ ላይ ትውልድን ማነጽ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

<u>አዲስ አበባ</u> ፡- ለነገ ጤነኛና ብቁ ሀገር ተረካቢዎችን ለማፍራት ዛሬ ላይ ትውልድን ማነጽ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለነገ ጤነኛና ብቁ ሀገር ተረካቢ ዜጎችን ለማፍራት ዛሬ ላይ የሚገኙ ወጣት ትውልዶችን በአካልና በስነልቦና ማነጽ ይገባል፡፡

ለዚህም ቢሮው የከተማው ወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እና ማህበራዊ ተሳትፎአቸውን በማረጋገጥ ጤነኛ፣ብቁና ንቁ ትውልድ ለመገንባት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡

በተለይም ወደፊት ሀገር ተረካቢ ወጣቶችና ሕፃናት በአዕምሮና በአካል የበለጸጉና የዳበሩ እንዲሆኑ ዓለም አቀፍ ሁኔታን የተረዱና ተወዳዳሪ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

አቶ በላይ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ በሚገኙ 114 የወጣት ሰብዕና መገንቢያ ማእከላት ውስጥ ከ18 በላይ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ በዚህም ወጣቱ አልባሌ ቦታ እንዳይውል ብሎም ራሱን በአካል ብሎም በአዕምሮ ብቁ እንዲሆን ይረዳል፡፡

በወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት ከሚሰጠው አገልግሎት አንዱ በሆነው በኪነጥበብ ዘርፍ የሀገርን ባህልና ወግ የተገነዘቡና አዳዲስ ሃሳቦችን የሚያፈልቁ ታዳጊዎች ታንጸው የሚወጡበት ነው ያሉት ኃላፊው፤ ይህም ባህልን፣ ሰላምና እና አንድነትን ለማጠናከር ያስችላል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም አባቶች ያስረከቡትን ባህልና ትውፊት ተቀብሎ የሚያስቀጥል እና የራሱን ታሪክ የሚጽፍ ትውልድ ለመፍጠር እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡

ተተኪ ስፖርተኞችን ከማፍራት እና ስፖርትን ባህል ያደረገ ማህበረሰብ በመፍጠር የከተማውን ስፖርት ወደላቀ ደረጃ ከማሸጋገር አኳያም የወጣቶች ስፖርት ማዘውተሪያዎችን የማስፋፋት ሥራ መሠራቱንም አስታውቀዋል፡፡

የስፖርት ማዘውተሪያ ከማስፋት አንጻርም በ2016 በጀት ዓመት 42 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ተገንብተው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፤ አጠቃላይ በከተማው 1242 የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

ሀገርን ለማስቀጠል የአስተሳሰብና የአመለካከት ጉዳይ ወሳኝ መሆኑን አቶ በላይ ጠቅሰው፤ በውይይት እና በሃሳብ የበላይነት የሚያምን ትውልድ በመፍጠር ህብረ ብሄራዊ አንድነትና ኢትዮጵያዊነትን ጠብቆ ማስቀጠል የሚችል ትውልድ ማነጽ ይገባል ብለዋል፡፡

በመሆኑም በአጠቃላይ ጉድለቶችን እያረመ ፤የነበሩ ጥንካሬዎች የሚያስቀጥል ብሎም መልካምና አዳዲስ ነገሮችን ለሀገር የሚያበረክት ሰርቶ የመለወጥ ትልቅ ራእይ ያለው ወጣት ትውልድ መፈጠር አለበት ብለዋል፡፡

ይህንን ባደረግን ቁጥር ሀገሩን የሚገነዘብ ትውልድን በመተካት በአብሮነት ኢትጵያዊነትን ከፍ በማድረግ በኩል ትልቅ ሚና ይኖረዋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ቢሮም ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግና ለነገ ሀገር ለመገንባት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በትኩረት የሚሠራ መሆኑን አቶ በላይ አስታውቀዋል፡፡

# በአዲስ አበባ እየተከናወኑ የሚገኙ የልማት ሥራዎች ለተቀሩ የአፍሪካ ከተሞች ምሳሌ ሆነው የሚታዩ ናቸው

## - የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ተሳታፊዎች

**ቃልኪዳን አሳዬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በአዲስ አበባ ከተማ እየተከናወኑ የሚገኙ ግዙፍ ፕሮጀክቶችና የኮሪደር ልማቱ ለቀሪው የአፍሪካ ከተሞች ለውጥ ተግባራዊ ምሳሌ ሆነው የሚታዩ መሆናቸውን የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ተሳታፊዎች ገለጹ።

የደቡብ አፍሪካ የኅብረት ሥራ አስተዳደርና ባህላዊ ጉዳዮች ምክትል ሚኒስትር ዲክሰን ማሴሞላ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በአዲስ አበባ ከተማ እያከናወነ በሚገኘው የኮሪደር ልማትና ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶች አመርቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል።

በከተማ ደረጃ የተከናወኑ ግዙፍ ፕሮጀክቶች በተሳካ ሁኔታ መፈጸማቸው የአመራሩን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ያሉት ምክትል ሚኒስትሩ፤ ታሪካዊው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ለሀገር ብቻ ሳይሆን ለመላው የጥቁር ሕዝቦች የተከፈለውን መስዋዕትነት በማጉላት የተገነባ መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል።

እንደ ዲክሰን (ዶ/ር) ገለጻ፤ ከተማዋ የአፍሪካ መዲናነቷን የሚመጥን፣ ለነዋሪዎቿ የሚመች የመሠረተ ልማትና የማህበራዊ አገልግሎቶችን እያዘመነች ነው። የኮሪደር ልማቱን ጨምሮ የከተማዋን ዓለምአቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያሳድጉ የልማት ሥራዎች መከናወናቸው የዜጎችን ኑሮ ከመቀየር ባለፈ የከተማዋን ገጽታ ለመገንባት ወሳኝ ሚና አላቸው። መንግሥት ለዜጎች የተሟላ አገልግሎት ለመስጠትና የሕዝቦቹን የአኗኗር ዘይቤ ለማሻሻል ብዙ ርቀት እየተጓዘ እንደሆን መመልከታቸውን የገለጹት ዲክሰን (ዶ/ር)፤ በመዲናዋ እየተካሄደ ያለው ግዙፍ ግንባታ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የዜጎቻቸውን የኑሮ ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል ጠቃሚ ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል። ምክትል ሚኒስትሩ ባደረጉት አጭር ቆይታ የሕዝቡን መስተንግዶ እና

ፎቶ፡- በረሀን ታደሰ



ዲክሰን ማሴሞላ (ዶ/ር)



ፖል ኢዱዴ

የተለያዩ ባህላዊ እሴቶችን መመልከታቸውን በመግለጽ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም እንቅስቃሴዎችን በማጎልበት እነዚህን በረከቶች መጠቀም እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

የአመራሩን ቁርጠኝነት በማድነቅ በመዲናዋ የተከናወነው የልማት ሥራ ወደ ሌሎች የክልል ከተሞች በማስፋፋት የሥራ እድል ፈጠራውን፣ የኢንቨስትመንትና የንግድ እንቅስቃሴውን ማጠናከር እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በናይሮቢ የኡጋንዳ ሪጅናል ሴንተር ፎር ሪሶርስ ማኔጅመንት ዳይሬክተር ፖል ኢዱዴ በበኩላቸው፤ በአዲስ አበባ የታየው አስደናቂ የከተማ ልማት ያላሰለሰ ጥረት ውጤት መሆኑን በማንሳት አፍሪካ ይህን ማሳካት እንደምትችል ማሳያ ነው ብለዋል።

አራት ኪሎን ጨምሮ በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች የተሠሩ የኮሪደር ልማት ሥራዎችን ተዘዋውረው መቃኘታቸውን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ በመልሶ ማልማት ሥራዎች ላይ ለሌሎች የአፍሪካ ከተሞች ትምህርት የሚሆን ጉልህ የልማት ተግባራትን እያከናወነች መሆኑን ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ የተሸከርካሪ፣ የእግረኛ፣ የብስክሌት መስመሮችንና ሌሎችም የተቀናጁ መሠረተ ልማቶች መዘርጋታቸውን አንስተው፤ ይህንን የመሰለ የልማት ሥራ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመሥራት ለውጥ ማምጣት ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነትን፣ ገንዘብን እና የሕዝቡን ፍላጎት የሚጠይቅ መሆኑን ጠቁመዋል።

ቁርጠኝነቱና ተነሳሽነቱ ካለ ምንም ነገር ማድረግ እንደሚቻል በአዲስ አበባ ከተማ በአጭር ጊዜ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች ትልቅ ማሳያዎች መሆናቸውን አመላክተው፤ የከተማዋ ለውጥ ለሌሎች ትምህርት የሚሰጥና መነሳሳትን የሚፈጥር እንደሆነም ተናግረዋል።

"ዘላቂ የከተሞች ልማት ለአፍሪካ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ 2063" በሚል መሪ ቃል የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም በዓድዋ ድል መታሰቢያ መካሄዱ የሚታወስ ነው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ወደ አዲሱ ዓመት ስንሻገር ጥንካሬያችንን አጎልብተንና ከድክመታችን ተምረን ሊሆን ይገባል!

ሰዓታት ቀናትን ወልደው፤ቀናት በወራት ተቀምረው አዲስ ዓመት ላይ ደርሰናል፡፡ ያለፈው አሮጌ ዓመትም ቦታውን ለአዲሱ ዓመት አስረክቦ ከነክፋትና ደግነቱ ላይመለስ ተሰናብቷል፡፡ አሮጌው ዓመትም በበጎም ሆነ በክፉ አሻራውን አሳርፎ አልፏል፡፡

አዲስ የገባው 2017 ዓ.ም ያለ2016 ዓ.ም እውን ሊሆን አይችልም፡፡ በ2016 በበጎም ሆነ በክፉ የተከሰቱ ጉዳዮች በ2017 በበጎም ሆነ በክፉ አሻራ ማሳረፋቸው አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህም በ2016 ዓ.ም እንደሀገር ያገኘናቸው ድሎችና ያጋጠሙን ተግዳሮቶች አዲስ በያዝነው ዓመት ላይ የራሱን አሻራ አሳርፎ አልፏል፡፡

እንደ ሀገር የነበሩን ጥንካሬዎች ለመጪው ጊዜ እርሾ ሆነው ያበረቱናል፤ከድክመቶቻችንም ተምረን የተሻለች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ስንቅ ሆነው ያገለግሉናል፡፡ በአጠቃላይ ጥንካሬዎቻችንን አጎልብተን፤ድክመቶቻችንን ቀርፈን የተሻለች ሀገር እንድትኖረንም በር ይከፍታል፡፡

የሸኘነው 2016 ዓ.ም እንደሀገር በርካታ ውጤቶች ያገኘንበትና በዚያው መጠንም የተፈተንበት ዓመት ነው፡፡ በ2016 ዓ.ም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ጎልታ የወጣችበት፣ በግብርና ምርት ውጤት ያመጣችበት፣ የድሆችን እንባ ያበሰችበትና ሰላምንም ለማጽናት ብዙ ርቀት የተጓዘችበት ዓመት ነው፡፡

በ2016 ዓ.ም ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግባለች፡፡ ከ300 ሚሊዮን ኩንታል ብዙም ዘሎ የማያውቀውን ዓመታዊ የምርት መጠን ወደ 600 ሚሊዮን ኩንታል ማድረስ ተችሏል፡፡ በቡና የውጭ ንግድ ግብይትም 1ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር በማግኘት ኢትዮጵያ አዲስ ታሪክ የጻፈችበት ዓመት ነው፡፡ በስንዴ እና በሩዝ ምርት የተገኘው ስኬትም ለመጪው ዘመን ተስፋ የሚሰጥ ነው፡፡

በ2016 ሀገራችን ካስመዘገበቻቸው ስኬቶች አንዱ በዓባይ ግድብ ዙሪያ የታየው አፈጻጸም ነው፡፡ በተሠራው ሥራም ተጨማሪ ሁለት ተርባይኖች ወደ ኃይል ማመንጨት ተግባር ገብተው ከሀገር አልፎ የጎረቤት ሀገራትንም በብርሃን ማድመቅ ችለዋል፡፡

ነሐሴ 17 ቀን 2016 ኢትዮጵያውያን በነቂስ ወጥተው ኢትዮጵያን በአረንጓዴ አሻራ ያለበሱበት ቀን ነው፡፡ በአንድ ጀንበር ከ600 ሚሊዮን በላይ ችግኝ በመትከል በጋራ ታሪክ ጽፈዋል፡፡ ይህም ስኬት 2017 አዲስ ዓመትን በተስፋ እንድንቀበለው አድርጎናል፡፡

በኮሪደር ልማት ፣ የባህር በር፣ በዲፕሎማሲው መስክ የተገኙ ውጤቶችም የጥንካሬዎቻችን መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ሆኖም ከእነዚሁ ጥንካሬዎቻችን ጎን ለጎን

ጦርነት፣ግጭት፣ መፈናቀል፣ ስደት፣ ድርቅ፣ የመሳሰሉት ችግሮች ኢትዮጵያን ፈትነዋታል፡፡ አለመተማመን፣መወነጃጀል፣ጥላቻና ቂምም የፖለቲካችን አንዱ መለያ ሆኖ አብሮን ቆይቷል፡፡ ይህም ሁኔታ በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ጦርነት እንዲቀሰቀስ፣ግጭት እንዲበራከት ፣ ሞትና የንብረት ውድመት እንዲከሰት አድርጓል፡፡ በዚህም በርካቶች ህይወታቸውን አጥተዋል፤ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ተሰደዋል፡፡

ይህ ታሪክ ግን አንድ ቦታ ማብቃት አለበት፡፡ የህዳሴ ግድብን የገነቡ ክንዶች፤በአንድ ጀንበር ከ600 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን የተከሉ እጆች፤የተራቡና የታረዙ ወገኖችን የታደጉ ስብናዎች ለግጭትና ለጦርነት ቦታ ሊኖራቸው አይገባም፡፡ በ2017 በቃ ልንላቸው ይገባል፡፡

ስለዚህም የመገጫጨት፣የመጠፋፋት እና የመገዳደል ታሪካችን ሊዘጋ ይገባል፡፡ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፣ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው፡፡ ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል፡፡ የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና፡፡ በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡

ስለሆነም የታሪካችን አንዱ ክፉይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል በአዲሱ ዓመት ልንጠቀምበት ይገባል፡፡


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኤሌክትሪክ- ለምናዘምናት ዓለም ቅንጦት ወይስ መሠረታዊ ፍላጎት?

**ፍሰሀ ጌታቸው**

የሰው ልጅ በምድር ላይ እንዲኖር ከሚያስችሉት መሠረታዊ ፍላጎቶች መካከል እንደ ምግብ (ውሃ)፣ አየር፣ መጠለያና አልባሳትን የመሳሰሉት በዋናነት ሲጠቀሱ የኖሩ ናቸው፡፡ ባለንበት ዘመን ከሰው ልጅ ዘመናዊ አኗኗር እና እየተላመደ ከመጣቸው በርካታ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አንጻር መሠረታዊ ፍላጎት ወደመሆን የተሸጋገሩና ከሕይወቱ ጋር የተሳሰሩ ሌሎች ጉዳዮችም አሉ፡፡

በተለይም ከሰው ልጅ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ ጋር በእጅጉ የተቆራኘውና ከፀሐይ ብርሃን ቀጥሎ ለምንኖርባት ዓለም እንደ ዓይን ብሌን በመሆን የሚያገለግለው፤ ለየትኛውም የምርምርና የፈጠራ ሥራ የጀርባ አጥንት የሆነው ኤሌክትሪክ ቅንጦት መሆኑ ቀርቶ መሠረታዊ ፍላጎት እየሆነ መጥቷል፡፡ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ካለው ወሰን አልባ አገልግሎቱ አንጻር አሁን ላይ ምሁራን ኤሌክትሪክን ከመሠረታዊ ፍላጎቶች ተርታ ሲያሰልፉት ይታያል፡፡

ዛሬ ዓለም ለደረሰበት የስልጣኔ ከፍታ እና ለሰው ልጆች አኗኗር መዘመን ድንቅ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ቀደምት ግኝቶች መካከል ኤሌክትሪክ ግንባር ቀደም ስለመሆኑ የሚከራከር አይኖርም፡፡ ኤሌክትሪክ የሰው ልጆችን ድካም አቅልሏል፤ ምርታማነትን አሳድጓል፤ ሀገራትን አስተሳስሯል፤ እድገታቸውን አፋጥኗል፤ ኢኮኖሚያቸውን አስወንጭፏል፤ ከፈጠራ ሥራዎችና ግኝቶች ጀርባም ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡ ዛሬም ኢትዮጵያ የነገ የማደግና የመበልጸግ ተስፋዋን ኤሌክትሪክ ላይ አድርጋ ከተፈጥሮ ሀብቶቿ ማለትም ከውሃ ፣ ከንፋስ፣ ከፀሐይ ብርሃን ፣ ከእንፋሎት የኤሌክትሪክ ኃይልን በማምረት ላይ ትገኛለች፡፡

የኢትዮጵያ ታዳሽ ኃይል ልማት ከአረንጓዴ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የሚቀዳ ስትራቴጂ ሲሆን ከውሃ 45ሺ ፣ ከጂኦተርማል 10ሺ ሜጋ ዋት እንዲሁም ከንፋስና ከፀሐይ 1ሺ ጊጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የሚያስችል እምቅ አቅም እንዳላት ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ እስካሁንም ከ5ሺ 200 ሜጋ ዋት በላይ ከውሃ፣ ከንፋስና ከእንፋሎት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ላይ ደርሳለች፡፡

ኢትዮጵያ አብሮ መልማትና ማደግን የምታስቀድም ሀገር በመሆኗ “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” እንዲሉ ለጋራ ዕድገትና ልማት ኃይልን በማቅረብ የቀጣናውን የእርስ በርስ ግንኙነት ለማጠናከርም ትሠራለች፤ እየሠራችም ትገኛለች፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ሪፖርት እንደሚያመለክተው ከ1 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ የሆኑ የዓለማችን ሰዎች አሁንም የኤሌክትሪክ አገልግሎት እያገኙ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ደግሞ ከ65 ሚሊዮን በላይ ሰዎች የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ አይደሉም፡፡

መንግሥታት ሕዝቦቻቸውን ከድህነትና ኋላቀርነት ለማላቀቅ በምትኩ ዕድገትና ብልጽግናን ለማምጣት በርካታ የልማት ሥራዎችን ያከናውናሉ፡፡ በአመዛኙ የልማት ሥራዎችን የሚያንቀሳቅሰው ሞተር ደግሞ ኤሌክትሪክ ነው፡፡ በዚህም መነሻነት ኢትዮጵያ የዜጎቿን ሕይወት ለመቀየር በግብርና፣ በመሬት አጠቃቀም፣ በደን ልማትና ጥበቃ፣ በኢኮኖሚያዊና የሥነ ምህዳር ሥርዓት ማጎልበት፣ በተሻሻሉና ተመራጭ የቴክኖሎጂ ውጤቶችና ኢንዱስትሪ ልማት፣ በትራንስፖርት አገልግሎትና ግንባታ ሥራዎች አጠቃቀምና በታዳሽና ንጹህ ኃይል ልማት ዘርፍ ላይ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ኢኮኖሚ መገንባት ከጀመረች ሰነባብታለች፡፡

አረንጓዴ ልማት ዛፎችን በመትከል ብቻ የሚተረጎም ሳይሆን የበካይ ጋዞችን ልቀት ማስቀረት የሚችሉ ታዳሽ ኃይሎችንም በማልማት ንጽህ አየር እንዲኖር ማድረግንም ያካትታል፡፡ የበካይ ጋዞች ልቀት ቀነሰ ማለት ዓለም በአየር ሙቀት መጨመርና እርሱን ተከትሎ በሚመጣው የኦዞን መሸንቆርና መሳሳት ችግር ሳይፈጠርባት ሚዛኗን ጠብቃ እንድትጓዝ ያደርጋታል፡፡ ተፈጥሮ ሚዛኗን ስትጠብቅ ወቅቱን የጠበቀ ዝናብ ይዘንባል፤ ወንዞች በልካቸው ይሞላሉ፤ የድርቅና የጎርፍ አደጋዎችም ስጋት መሆናቸው ይቀንሳል፡፡ የበካይ ጋዝ ልቀትን ለመቆጣጠር ከሚያስችሉ ጉዳዮች አንዱ ለኢንዱስትሪዎችና ለተለያዩ አገልግሎቶች የምንጠቀመውን ኤሌክትሪክ ከታዳሽ ኃይል ማልማት የሚለውም ኢትዮጵያ የምትከተለው ፖሊሲዋ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገትን ማረጋገጥ እንዲያስችላት በኃይል ልማቱ ዘርፍ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ግዙፍ የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማቶችን መገንባት ችላለች፡፡ ከእነዚህ መካከል የዘመናት ቁጭት የወለደው የሕዝቦችን የመልማት አቅም የሚወስነውና የይቻላል ስሜት ማሳያ የሆነው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አንዱ ነው፡፡

አባቶቻችን ልዩነታቸውን ወደ ጎን ብለው የዓድዋ ጦርነትን ድል እንዳደረጉ ሁሉ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብም እንድንለማና እንድናድግ ለማይፈልጉ ኃይሎች በራስ አቅም፣ ገንዘብና ጉልበት መሥራት እንደምንችል ያሳየንበት፣ የዚህ ዘመን ትውልድ ዐሻራ ነው፡፡ ይህም በልማቱ ላይ የተደገመ የአልሸነፍ ባይነት ዳግማዊ የዓድዋ ድል ተምሳሌት ነው፡፡

ይህ ፕሮጀክት ከሌሎች ግድቦች ልዩ የሚያደርገው በውስጥና በውጫዊ ኃይሎች ጠንካራ ፈተና የገጠመውና ፈተናውን አሸንፎ ከስኬት የደረሰ መሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንደሌሎች ሀገራት የራሷ ሀብት በሆነው በዓባይ ወንዝ ላይ ተጠቃሚ እንዳትሆንና የበይ ተመልካች ሆና እንድትቀር ለዘመናት ይደርስባት የነበረውን ክልከላ “ጆሮ ዳባ ልበስ” በማለት የማይደፈረውን በመድፈር፣ የማይቻለውን በመቻል ለውጤት ማብቃት ችላለች፡፡

ከውስጣዊ ችግሮች አንጻርም የግድቡን የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራዎች ለመሥራት ኃላፊነት ወስዶ የነበረው የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) በፈጠረው የጊዜ መጓተት፣ የጥራት መጓደል፣ የአስተዳደር እና የብልሹ አሠራር እንከን፤ ታላቁ የህዳሴ ግድብ በተባለው ጊዜ ተጠናቆ ጥቅም ላይ የመዋሉን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ነበር፡፡

ይሁንና በ2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሰማይ ስር የተከሰተው ሀገራዊ የመንግሥት ለውጥ ለህዳሴው ግድብ መድህን እንደነበር የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡ በተለይ በግድቡ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ሥራዎች ላይ ተፈጥሮ የነበረውን ችግር ለመፍታት የለውጡ መንግሥት የሥራ ተቋራጩን የመቀየርና ሥራውን በጥብቅ ዲስሊፕሊን መምራት በመቻሉ ፕሮጀክቱ ከነበረበት ህመም ድኖ ለዛሬው ውጤት መብቃት ችሏል፡፡

የታላቁ የህዳሴ ግድብ ከኃይል ጠቀሜታው ባሻገር ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ሃይማኖት፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ ክልል ሳይለይ የሕዝቦችን አንድነት የፈጠረ፣ የአልሸነፍ ባይነትን ክንድ ያሳየ፣ የዘመናት ቁጭትን የመለሰ፣ የዜጎችን ገንዘብ፣ ጉልበት፣ ሃሳብና እውቀትን ያሰባሰበ፣ የቁጠባ ባህልን ያዳበረ፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገራት ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠረ፣ ለአፈርና ውሃ ጥበቃ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ፣ ለቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር በር የከፈተ፣ የሀገራችንንም የመደራደር አቅም ያሳደገ፣ ለዓሳ ሀብት፣ ለቱሪዝም ልማት፣ ለጥናትና ምርምር ዕድል የሰጠ እና የይቻላል መንፈስ የተተረጎመበት ፕሮጀክት ነው፡፡

የለውጡ መንግሥት ሀገር መምራት በጀመረበት ማግስት ለህዳሴ ግድብ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረትና ድጋፍ አበው “የምሥራች ፍሬ ቀመስኩ” እንዲሉ ከሚጠበቀው 5ሺ 150 ሜጋ ዋት ውስጥ በ2014 ዓ.ም በወርሃ የካቲት 375 ፣ በወርሃ ነሐሴ 375 በድምሩ 750 ሜጋ ዋት በማመንጨት ኢትዮጵያ “የህዳሴው ግድብ የምሥራች ፍሬን” መቅመስ ችላለች፡፡

በዘንድሮ የክረምት ወቅትም ሁለት ተርባይኖች ኃይል ወደ ማመንጨት ገብተዋል፡፡ በመጪው ታህሳስ ወርም ኃይል የሚያመነጩ ተርባይኖች ቁጥር ወደ ሰባት እንደሚደርስ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሰሞኑ በነበራቸው የሥራ ጉብኝት ገልጸዋል፡፡ የህዳሴው ግድብ ሥራ በመጪው ዓመት ሙሉ ለሙሉ የሚጠናቀቅ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡ እንግዲህ ይህ ግድብ ኢትዮጵያውን አቅማቸውን ገንዘባቸውንና ሃሳባቸውን አስተባብረው የወለዱት አንጋፋው ልጃቸው እንደሆነ ዓለም የሚያውቀው ሀቅ ነው፡፡

ይህ ታላቅ ፕሮጀክት ጠንካራ ህብረ-ብሄራዊ አንድነትን ያጎለበተ፣ የሀገርን ገጽታና ኢኮኖሚም የገነባ ነው፡፡ መንግሥት ፕሮጀክቱ በትክክለኛ የጥራት ደረጃና በተያዘለት ጊዜ እንዲከናወን በማገዝ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሥራ አመራር ቦርድንና ተቋሙን እንደ አዲስ በማዋቀር፣ በአዲስ የተዋቀሩት የሥራ አመራር ቦርዱና ተቋሙ ሥራው በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመራ በማድረግ፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ብሄራዊ ማስተባበሪያ ምክር ቤትም እንዲሁ ሕዝባዊ ድጋፍ በማሰባሰብ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ከሁሉም በላይ የግድቡ ባለቤት የሆነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ (እናቶች፣ አባቶች፣ ወጣቶች፣ ሕፃናት) ተመራማሪዎች ሙያተኞች፣ ዲፕሎማቶች፣ ዲያስፖራዎች ወዘተ የነገ ተስፋችንን የሚያለመልመውን ታላቁ ግድብ በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በእውቀት የማይተካ ድጋፍ አድርገናል፤ያም ብቻ ሳይሆን ላባችንን አንጠፍጥፈን ደማችንንም አፍስሰን የመጨረሻው ምእራፍ ላይ አድርሰነዋል፡፡ ዛሬ የምሥራች ፍሬውን ቀማምሰናል፤ ነገ ደግሞ ተዝቆ ከማያልቀው በረከቱ ጠግበን ለጎረቤቶቻችንም በመትረፍ እጅ ለእጅ ተያይዘን ለምንገነባት ዘመናዊዋ ዓለም በጋራ እንጠቀምበታለን፡፡

# የቀጣዩ ዘመን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የኢንቫይሮመንታል ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ምንተስኖት ግዛው (ዶ/ር)፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ላይ መሥራት ከሥራ ዕድል ፈጠራ ባሻገር ሀገሪቱ ለነዳጅ የምታወጣውን ወጪ መቀነስ ያስችላታል ይላሉ።

ሀገሪቷ ያላትን የጸሀይና ነዳጅ ሀብቶችን በመጠቀም በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል አቅርቦትን ለማሻሻል መሥራት ይገባል ያሉት ምንተስኖት (ዶ/ር)፣ከዋናው የኤሌክትሪክ መስመር(ግሪድ) የራቁ ቦታዎች ላይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ እንዲስፋፋ የሚያስችል የመሰረተ ልማት ዝርጋታ ሥራዎችም ትኩረት ይፈልጋሉ ሲሉ ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ የትራንስፖርት ዘርፉ ከውጪ በሚገባ ነዳጅ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዓመት ለነዳጅ ከውጪ ለማስገባት ከፍተኛ የሆነ የሀገሪቱ ሀብት ወጪ እንደሚደረግበት ይገልጻሉ።

የተጀመረውን የኤሌክትሪክ ተሽከርካዎች በስፋት ወደ ገበያው የማስገባት ተግባር በማጠናከር ነዳጅን በታዳሽ ኃይል መተካት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የተለያዩ የኃይል ማምረቻ አማራጮችን በመጠቀም በቻርጅ ለሚሰሩ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ማዋል ይጠይቃል ሲሉ ያስረዳሉ።

በመንግሥት በኩል ለዘርፉ ማበረታቻና ድጋፍ በማድረግ፣ችግሮችን በመፍታት በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል አቅርቦት ማሳደግ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በማበራከት የትራንስፖርት ዘርፉ የሚያመነጨውን በካይ ጋዝን፣ ከአየርና የድምጽ ብክለትን መከላከልን ጨምሮ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠንና ለሥራ እድል ፈጠራ አበርክቶ እንዳላቸውም ይገልጻሉ።

አክለውም፤ ዘርፉ ለሀገሪቱ የውጪ ምንዛሬን ማምጣት ባይችልም እንኳን ለነዳጅ የሚወጣውን የወጪ ምንዛሬ የሚያስቀር በመሆኑ ኢንዱስትሪውን መንግሥት መደገፍ አለበት ይላሉ።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም ሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን፣ለነዳጅ የሚውለውን የውጪ ምንዛሬ ለማስቀረት፣ በመተንፈሻ አካላት ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው የሚሉት ደግሞ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ይዘንጋው ይታይህ ናቸው።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን የበለጠ ሥራ ላይ ለማዋል መንግሥት የፖሊሲና ስትራቴጂዎች፣መመሪያዎችን ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲ፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችና የተሽከርካሪዎች ቻርጅ ስታንዳርድን ጨምሮ ዘርፉን ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራት እየተከናወነ መሆኑን ይገልጻሉ።

መንግሥት የግል ባለሀብቱን ለማበረታታት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ነው ያሉት አቶ ይዘንጋው፤ ሙሉ በሙሉ ተፈታትተው የሚገቡ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ መፈቀዱን ይናገራሉ።

በዘርፉ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ቻርጅ ማድረጊያ መሳሪያዎች ተግዳሮት መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በመሆኑም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች መስፋፋት ላይ ተግዳሮት መሆኑን ያስረዳሉ።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ቻርጅ ማድረጊያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ መፈቀዱን የገለጹት አቶ ይዘንጋው፤ ባለሀብቱን ለመሳብ በመሬት አቅርቦትና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ላይ እየተሠራ መሆኑንም ይገልጻሉ።

የመሰረተ ልማት መስፋፋት ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች መስፋፋት ከፍተኛ አበርክቶ እንዳላቸውና ደረጃቸውን ያልጠበቁ ቻርጅ ማድረጊያ መሳሪያዎች ወደ ሀገር እንዳይገቡ ለማድረግ የሚያስችል ስታንዳርድ እየተዘጋጀ መሆኑንም ያስረዳሉ።

የኖክ ነዳጅ ኩባንያ ሥራ አስፈጻሚና የአይል ካምፓኒዎች ማህበር ፕሬዚደንት አቶ ታደሰ ጥላሁን ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በሀይድሮ ፓወር የተመረተውን ኃይል በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻሉ።

ኖክ የነዳጅ ኩባንያ ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የሚውሉ መሠረተ ልማቶችን በየነዳጅ ማደያዎቹ ሁሉ እንዲዘረጋ ማድረግ ላይ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ ነዳጅ እንደሚቀርበው ሁሉ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቻርጅ እንዲኖር በማድረግ ለተሽከርካሪዎች ለማቅረብ የሚያስችል አሠራር እንደሚዘረጉ ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ እያደገች የምትገኝ ሀገር በመሆኑዋ ከፍተኛ የኃይል ፍጆታ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ታዳሽ ኃይልን በስፋት ማሳደግና በዘርፉ የግሉም ባለሀብት ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ።

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ሰሃረላ አብዱላሂ በበኩላቸው፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ለነዳጅ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ለመቀነስ ይረዳል ሲሉ ይገልጻሉ።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ በስፋት ሥራ ላይ እንዲውል ጥናት ላይ የተመሰረቱ ሥራዎችን ማካሄድ ላይ እየተሠራ መሆኑንም ይገልጻሉ።

መሰረተ ልማት ግንባታ በሰፊው ማካሄድ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን ለማስፋት ወሳኝ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ ለዚህም እንደ ሀገር የተለያዩ ሀገራትን ተሞክሮ በመቅሰም ወደ ሥራ ተገብቷል ሲሉ ይናገራሉ።

ባለሥልጣኑም ዘርፉ ዝቅተኛ ታሪፍ የሚኖርበትን አሠራር ለመዘርጋት የግሉን ዘርፍ ለማበረታታት እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ልማት የግሉ ዘርፍ በስፋት እንዲሳተፍ የሚያደርገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን እውን ለማድረግ ባለሥልጣኑ የድርሻውን እየተወጣ መሆኑንም ተናግረዋል።

# ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የዲጂታል ክህሎት በዋናነት መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት፣ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅሞ ሥራ መሥራት መቻልንና መተግበሪያዎችን ማልማትን ያጠቃልላል የሚሉት ዶክተር አብዮት፤ መሠረታዊ የኮምፒውተርን ክህሎት ሁሉም ሰው ሊያውቀው ይገባል። በዚህም አብዛኛው ሀገራት ዜጎቻቸው መሠረታዊ የኮምፒውተር ክህሎት እንዲኖራቸው እያደረጉ መሆኑን ያመላክታሉ።

ወደሥራ የሚሰማራው የሰው ኃይል ውጤታማ ሥራን ማከናወን የሚችለው ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ሲጠቀም በመሆኑ፤ የዓለም ሀገራት የትምህርት ሥርዓት የዲጂታል ክህሎትን ያካተቱ ናቸው። በዚህም ማንኛውም ሰው በሚያልፍበት የትምህርት ተቋማት በቂ የዲጂታል ክህሎት አግኝቶ እንዲወጣ እያደረጉ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

ሀገራት ራሳቸውን ለመጠበቅ፣ ጥቃት ለማድረስ እና ኢኮኖሚያዊ እድገታቸውን ለማፋጠን አዳዲስ መተግበሪያዎችን የሚያለሙ እና በቂ የዲጂታል ክህሎት ያላቸው ዜጎችን ማፍራት ላይ ትኩረት ማድረጋቸውን ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትከተለው የቆየችው የዲጂታል ፖሊሲ ውድድርን የማያበረታታ መሆኑ፤ መሠረተ ልማት አለመስፋፋቱ እና ኢትዮ ቴሌኮም በገበያ የሚመራ ባለመሆኑ ወደኋላ እንድትቀር ምክንያት መሆኑን ያብራራሉ።

ኢትዮጵያ ወደኋላ የቀረችበትን የቴክኖሎጂ ዘርፍ ችግሮች በመፍታት ከአደጉ ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ለማድረግ የቴሌኮም ሴክተሩን ለገበያ ክፍት የማድረግ፣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን ወደገበያ የማስገባት፣ የትምህርት ካሪኩለሙን የመቀየር፣ በመንግሥት አሠራር ዲጂታል አሠራርን አስገዳጅ ማድረግ፣ የዲጂታል ክፍያዎችን በዲጂታል የማድረግ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ያስረዳሉ።

በቀጣይም እነዚህን እና ሌሎች ሥራዎችን ትኩረት በመስጠት መተግበር ከተቻለ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ካደጉ ሀገራት ተርታ መሰለፍ ትችላለች ሲሉ ያብራራሉ።

ሌላኛው የቴክኖሎጂ ባለሙያ ካሳሁን ጉተማ በበኩላቸው፤ አሁን ያለንበት ዘመን የቴክኖሎጂ እንደመሆኑ መጠን ኢንዱስትሪዎች፣ የወጪና ገቢ ንግዱ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች እና ሌሎች ዘርፎች በቴክኖሎጂ እየተሳሰሩ ነው ይላሉ።

የተለያዩ ዘርፎች ከቴክኖሎጂ ጋር መተሳሰራቸው መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት፣ ጊዜን ለመቆጠብ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመንና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል።

የዓለም ሀገራት የቴክኖሎጂ ዘርፍን የመወዳደሪያ መስፈርት አድርገው በትኩረት እየሠሩበት መሆኑን በመግለጽ፤ የግብርና፣ የጤና፣ የፋይናንስ፣ የትምህርት እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ከቴክኖሎጂ ጋር ተሳስረው አገልግሎት አሰጣጣቸውንና መረጃ አያያዛቸውን በማዘመንና በማቀላጠፍ ምርትና አገልግሎታቸውን በማሳደግ ተወዳዳሪ ሊሆኑ እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ባለሙያው እንደሚሉት፣ የኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ አቅምና አጠቃቀም ካለፉት ጊዜያት እየተሻሻለ ቢመጣም፤ አሁንም ሰፊ ሥራን ይጠይቃል። መንግሥት ዘርፉን ለማሳደግ የጀመራቸው ሥራዎች መበረታታት እንዳለባቸው እና ከሕፃናት ጀምሮ በሁሉም የእድሜ ደረጃ ለሚገኙ ሰዎች ቴክኖሎጂን በማስረዳት የእውቀት ሽግግር ማድረግ እንደሚገባ ይናገራሉ።

የቴክኖሎጂውን ዘርፍ ለማሳደግ መንግሥት የልማት አጋሮች፣ የግል ድርጅቶች ትምህርት ቤቶች እና እያንዳንዱ ማህበረሰቡ ኃላፊነት ወስደው ሊሠሩ ይገባል። ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ ማድረግ ከተቻለ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ እድገት ማሳለጥ፣ በሁሉም ዘርፎች ብቁ የሆነ ትውልድን ማፍራት እና ኢንቨስተሮችን መሳብ ያስችላል ይላሉ።

ዲጂታል ኢትዮጵያ የመንግሥትን፣ የግሉን ዘርፍና የልማት ድርጅት ተዋንያንን በአንድ ላይ በማሰባሰብ፣ መሠረታዊ የዘርፍ ተነሳሽነትን በመለየት የሀገሪቱን የዲጂታል ኢኮኖሚ ጉዞ የሚያሳልጥ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በኃላፊነት ሊሠሩ ይገባል።

# ግብርናን እያሻገረ ያለው የግብዓት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እየተሠራ ነው።

ሀገሪቱ ምርታማነትን የሚሻገር የግብርና ግብዓትን በመጠቀም በበጋ መስኖ፣ በበልግ እርሻ፣በመኸርና በኩታገጠም ልማት የተትረፈረፈ ምርት የማግኘት ስራ እያከናወነች ነው።

የግብርናውን ምርታማነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በብዙ ሚሊዮን ኩንታል የሚቆጠር የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው።

የአምራች ክፍሉ የአፈር ማዳበሪያን የመጠቀም ባህሉ ከዓመት ወደ ዓመት እየያደገ በመምጣቱ ትናንት በአስር ሺህና በሚሊዮን ግዥ ይፈፀምና ተደራሽ ይደረግ የነበረው ዛሬ ላይ ሁለት አስርት ሚሊዮን ኩንታል ደርሷል።

የዩክሪንና የሩስያ ጦርነት፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ብጥብጦች የአፈር ማዳበሪን በስፋት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ትልቅ ተግዳሮቶች ቢሆኑም ቀላል የማይባል መስዋእት በመክፈል ምርታማነትን የሚያሻግር ግብዓት ለአምራቹ ማህበረሰብ ተደራሽ ተደርጓል።

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)፤ በግብርና ዘርፉ ላይ እየተሠራ ያለው የማዘመን፤ በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ሥራ እንዲሁም የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ተደራሽነት ሀገሪቱን ወደ ማክሮ ኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የሚያስገባ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ለግብርናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማቅረብ፤ አሰራሩን በማዘመን ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ ትልቅ ውጤት እያስገኘ እንደሆነም ይናገራሉ። ባለፉት ዓመታት በግብርና ግብዓቶች አቅርቦት፤ ስርጭትና አጠቃቅም የነበሩ መሠረታዊ ችግሮችን በመሠረታዊ ለውጥ በመፍታት ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉም ይገልጻሉ።

የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚጠቅሙ ግብዓቶች ውስጥ ዋናኛው የአፈር ማዳበሪያ ሲሆን፤ አጠቃቀሙና ፍላጎቱ በየዓመቱ እየጨመረ መጥቷል።

የዩክሬንና የሩሲያ ጦርነት፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ውዝግብ የአፈር ማዳበሪን ገብይቶ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ትልቅ ተግዳሮት ሆኗል፤ የሀገር ውስጥ ግጭቱም የተገዛውን የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሮች በወቅቱ ተደራሽ ለማድረግ የሚፈትን ነው፤ የሀገር ውስጥና የውጪ ተግዳሮቶችን በመቋቋም ግብዓትን በሰፊው ተደራሽ የማድረግ ሥራ ውጤታማ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

ባለፉት ዓመታት ለአፈር ማዳበሪያ የአቅርቦትና ስርጭት እጥረት መንስኤ የነበሩትን የግዥ ሥርዓት መመሪያ፤ የትራንስፖርት እጥረት፣ በቅንጅት ያለመሥራት ችግር፣ የቀረበውን ግብዓት በወቅቱና በጊዜው ያለማሰራጨትና መሰል ተግዳሮቶችን በመፍታት ምርትና ምርታማነትን የሚያሻገር አቅርቦት ተደራሽ የማድረግ ሥራ እየተከናወኑ ነው ይላሉ።

የአፈር ማዳበሪያ የግዥ ሥርዓት የሀገርን ጥቅም ባስከበረ መልኩ በማከናወን የሀገርን እድገት የማፋጠን ሥራ በዘርፉ በኩል እየተሠራ ነው ሲሉ ይጠቁማሉ።

ኢትዮጵያ በ2013 ዓ.ም በጣም ትልቅና ብዙ የተባለውን የአፈር ማዳበሪያ የገዛችበት ዓመት ነበር፤ በወቅቱም 18 ሚሊዮን ኩንታል ነበር የገዛችው፤ በሀገሪቱ የምርትና ምርታማነት፣ የአፈር ማዳበሪያ አጠቃቀም ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን 20 ሚሊዮን ኩንታል አፈር ማዳበሪያ ገዝታለች፤ ለ2017/18 ዓ.ም የምርት ዘመንም 25 ሚሊዮን ኩንታል ለመግዛት አቅዳ እየሠራች ትገኛለች።

አርሶ አደሮች ብርዱ ሳይበግራቸው፣ ድካም ሳያስንፋቸው፤ ያለሰለሱትን የእርሻ ማሳ በወቅቱ በዘር እንዲሸፍኑ የአፈር ማዳበሪያ ግብዓትን ግዥ በመፈፀም በሰዓቱ እንዲሰራጭ የማድረግ ሥራ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፤ በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመንም በአቅርቦትና በተደራሽት በኩል ትልቅ ውጤት ተመዝግቧል ሲሉ አብራርተዋል።

በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን የቀረበው የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ከ2014/15 ዓ.ም የምርት ዘመን ጋር ሲነፃፀር የስድስት ሚሊዮን ኩንታል ጭማሪ ያሳየ ሲሆን ለ2017/18 ዓ.ም የታቀደው የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ከ2016/17 ዓ.ም የአምስት ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ እንደሚኖረው በዕቅዱ ተመላክቷል።

የሀገሪቱን ምርትና ምርታማነት ለማሻገር የሚጠቅሙ ግብዓቶችን ገዝቶ በወቅቱና በጊዜው የማሰራጨት ስራ ብቻ ሳይሆን ግብዓቶችን በቀላል ዋጋ በመግዛት፣ በፍጥነት ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ተጠቃሚነቷን የማስጠበቅ ስራ እየተሰራ ነው፤ እየተሰራ ባለውም ስራ በ2016/17 ዓ.ም ከአፈር ማዳበሪያ ግዥ ከ24 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን ተችሏል ይላሉ።

የ2017/18 ዓ.ም ምርትን ለማሳደግ የታቀደውን 25 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው፤ ተገዝቶ ሲቀርብ ክልሎች በወቅቱና በጊዜ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ ከወዲሁ መዘጋጀት እንዳለባቸው ተጠቁሟል።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሀገሪቱ ግዥ ፈፅማ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባውን የአፈር ማዳበሪያ ለታለመለት ዓላማ በማዋል ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው። የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የዜጎችን የሥነ-ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል አንዱ የአፈር ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በበቂ ሁኔታ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ነው ይላሉ።

የግብርና ምርታማነትን የሚያሳድገውን የአፈር ማዳበሪያ ግብዓትን በጊዜው፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሮች በማድረስ ኢኮኖሚያዊ እድገት እየተመዘገበ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ከክልሎች የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት ከማሰባሰብ እስከ ስርጭት ድረስ እየተሠራ ያለው ሥራ ውጤታማ ነው፤ የበጋ መስኖ ልማት፣ የአርሶ አደሮች የአፈር ማዳበሪያ የመጠቀም ፍላጎት መሠረት ያደረገ የግብዓት አቅርቦት ሥራ እየተከናወነ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

ሀገሪቱ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት የመግዛት አቅሟ እያደገ መጥቷል፤ይህም ምርትና ምርታማነትን እያሳደገ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

ከዓመት ወደ ዓመት አፈር ማዳበሪያ የግብዓት አቅርቦት በማሳደግ፤ አርሶ አደሮች ፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች ጥራት ያለው ምርት እያመረቱ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የአፈር ማዳበሪያን በወቅቱ በማስገባት ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ ሥራ ከእለት ወደ ዕለት እያደገ፤ እየተሻሻለ ነው፤ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት የጀርባ አጥንት ግብርና በግብዓት አቅርቦት ተደራሽነት፤ በቴክኖሎጂ ድጋፍ በማጠናከር ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ይጠቁማሉ።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ወጣቶችና አዲስ ዓመት



ወጣት ሔኖክ



ወጣት ጫላ

**ክብረአብ በላቸው**

አሮጌው ዘመን በአዲሱ የመቀየሩን ብሥራት አብሣሪው የአዲስ ዓመት (ዕንቁጣጣሽ) በዓል፤ በእኛ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ሥፍራ ከሚሰጣቸው በዓላት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው። የጨለማ ተምሳሌት የሆነው ጭጋጋማው የክረምት ወቅት አልፎ፣ ቀን ከሌሊት ይዘንብ የነበረው ዝናብና አስገምጋሚው መብረቅ ጋብ የሚልበት፣ ምድር በዐደይ አበባ ተጥለቅልቃ በልምላሜ የምትታይበት፣ አሮጌው ዘመን ወደ ኋላ ተትቶ አዲሱ ሊተካ "እዮሃ አበባዬ" የሚባልበት በዓል በመሆኑ በብዙዎቻችን ዘንድ የተለየ ትርጓሜ ይሰጠዋል።

አዲስ ዓመት ሲመጣ በዓሉን በአዲስ መንፈስ እና ስሜት ለመቀበል የሚደረገው የቤት ጽዳትና ዕድሳቱ፣ ልብስ አጠባውና አሮጌውን በአዲስ ለመቀየር የሚከናወነው ግብይት፣ የሳር፣ የአደይ አበባ ጉዝጓዝ፣ የጠላው፣ የጠጁ፣ የዶሮው፣ የዳቦው ዝግጅት እና አጠቃላይ ሽር ጉዱ፤ ዕለቱን በይበልጥ እንድንናፍቀውና ከአሁን አሁን ዐውደ ዓመቱ በደረሰ እያልን በጉጉት እንድንጠባበቀው የሚያደርግ ስሜት ይፈጥርብናል።

ታዲያ አሮጌ ያልነው ዘመን አብቅቶ በአዲስ መተካቱን ከሚያበስሩን ከእነዚህ ማኅበራዊና ትውፊታዊ የዓውድ ዓመት ሥነ ሥርዓቶች በተጨማሪ፣ ተፈጥሮም እራሷን በውበት አሰማምራ የአዲስ ዓመትን መጥባት የምታመለክትባቸው ልዩ ልዩ መገለጫዎች አሏት።

አዲስ ዓመት ሲመጣ ሜዳው፣ ሸንተረሩ፣ ጋራና ሸለቆው በውብ የአበቦች ፍካት ይታጀባል፤ የአዋፋት ዝማሬ በየቦታው ይሰማል፤ ዐደይ አበባም ለረጅም ወራቶች ሳትታይ ቆይታ ወቅቱን ተከትላ በየስፍራው ብቅ ማለቷን ትጀምራለች፡፡ የክረምቱን ማብቃትና የአዲሱን ዘመን መግባት የምታበስረው የመስቀል ወፍም በውብ ላባዋ ደምቃ ከተደበቀችበት በመውጣት የምትታይበት ወቅት ነው።

እኛም የ2017 አዲስ ዓመትን መነሻ በማድረግ በተለይ አዲሱን ዓመት ወጣቶች በምን መልኩ መቀበል አለባቸው እነርሱስ በምን መልኩ ለመቀበል አስበዋል በሚል በተለያየ የሥራ ዘርፍ ከተሰማሩ ወጣቶች ጋር ቆይታ አድርገናል።

ወጣት ጫላ አሰፋ ይበላል። በሙያው ኢንጂነር ነው። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሰላም ማህበር መስራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው። እርሱ እንደሚናገረው፤ አዲስ ዓመት ሲመጣ በአሮጌው ዓመት ለመሥራት አስበን ማሳካት ያልቻልናቸው ሥራዎች በአዲስ ጉልበትና በአዲስ እስትራቴጂ ለመሥራት ዕድል የምናገኝበት ዓመት ነው ይላል።

አዲስ ዓመትና ወጣትነት በባህርዩ ተመሳሳይነት አለው የሚለው ወጣት ጫላ፤ ወጣት የአዲስ ሀሳብ የፈጠራ ባለቤት ትኩስ ኃይል ነው። ይህ የወጣት ጉልበት ሀገራችን በአግባቡ ከተጠቀመች ሕዝብ የሚፈልገውን ነገር ማምጣት ይቻላል፤ ስለዚህ በአዲሱ ዓመት የወጣቱን እውቀትና ጉልበት በመጠቀም ለመለወጥ መዘጋጀት አለብን ይላል።

ወጣት አዲስ አሰራር ተቀብሎ ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጐት ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ስለመሆኑ የሚናገረው ጫላ፤ በአዲሱ ዓመት በተለያየ መስክ የተሰማሩ ወጣቶች ያላቸውን ሀሳብ በመሸጥ መለወጥ እንዲችሉ አቅሙ ያላቸው አካለት ከጎናቸው በመሆን ሊያግዟቸው ይገባል ይላል።

በሀገራችን ባለማወቅ ያሳለፍናቸው ጎዶሎዎች አሉ የሚለው ወጣት ጫላ፤ ይህንን ገደል በድልድይ ማገናኘት ከወጣቶች ይጠበቃል፤ በተጨማሪም በማወቅም ሆኖ ባለማወቅ የተገነቡ የጥላቻና የፍራቻ ግንቦች አሉ፡፡ ይህንን ግንብ በመናድ የሀገራችን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትና ፍቅር እንዲያድግ ማድረግ ከወጣቶች የሚጠበቅ በመሆኑ በአዲሱ ዓመት በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የእርስ በእርስ መተሳሰብ እንዲያድግ መሥራት አለባቸው ይላል።

ሀገሪቱ ወደፊት ሆና ማየት የምንፈልጋትን እንድትሆን በርካታ ሥራ ከወጣቶች ይጠበቃል፤ ይህንን ከባድ ኃላፊነት ለመወጣት በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ እውቀት፣ በአዲስ ጉልበት ተነስቶ መሥራት ያስፈልጋል የሚለው ወጣት ጫላ፤ ብዙ ግዜ ወጣቶች የነገ ሀገር ተረካቢ ይባላሉ ነገር ግን ወጣቶች የነገ ሀገር ተረካቢ ብቻ ሳይሆኑ የዛሬውን ሀገር ተረክበው ማስተዳደርና መኖር ይችላሉ ይላል።

ወጣቶች መገፋፋትን ትተን መቀራረብን፣ ጥላቻን ትታን ፍቅርን፣ መስበክ አለብን የሚለው ጫላ፤ ከነጠላ ትርክት ወጥተን ወደ ወል ትርክት መጓዝ መቻል አለብን የሚለው እምነት አለው፡፡ ይህ ሲሆን ሀገራችን ተለውጣ የምናይበት ግዜ እሩቅ አይሆንም ለዚህ ሁላችንም የሚጠበቅብንን ሚና መወጣት አለብን ይላል።

በኢትዮጵያ የሕዝብን ኑሮ መቀየር የሚችሉ የልማት ሥራዎች እየተሰሩ ስለመሆኑ የሚናገረው ወጣት ጫላ፤ ይህንን ልማት ለማስቀጠል ወጣቱ በባለቤትነት መሥራት አለበት፤ መንግሥትም ወጣቱ መሥራት እንደሚችል አምኖ ዕድል በመስጠት ወጣቱን አሳታፊ መሆን እንዳለበት ያስረዳል።

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮችን ለመቅረፍ ከመንግሥት ባሻገር ወጣቱ ኃላፊነት እንዳለበት የሚናገረው ጫላ፤ በሰላም ግንባታ ሂደት የራሳቸውን ድርሻ በመውሰድ የተረጋጋች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ይናገራል።

በኢትዮጵያ በእስከአሁኑ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣቶች ተጎጂ ሆነው ቆይታዋል የሚለው ጫላ፤ ጉዳቱ የሚደርሰው ወጣቶች ባልፈጠሩትና ባላደረጉት ነገር ነው፤ ስለዚህ ይህንን ችግር ለመፍታት ወጣቶች መነጋገርና መወያየት አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ ምክክር መልካም ዕድል ሆኖ መጥቷል በዚህ ሂደት በንቃት በመሳተፍ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ መሥራት አለባቸው ይላል።

እኛው ተመካክረን ለራሳችን ችግር መፍትሔ ማበጀት ከልቻልን ማንም መጥቶ ችግራችንን ሊፈታልን አይችልም የሚለው ወጣት ጫላ፤ ወጣቶችን የገፋ ወይም በተገቢው መልኩ ያላሳተፈ ሀገራዊ ምክክር ደግሞ ውጤታማ መሆን አይችልም ይላል፡፡ የተለያዩ ሀገራት ስኬታማ ሀገራዊ ምክክር አድርገው ችግሮቻቸውን መፍታት የቻሉት ወጣቶችን በማሳተፍ ነው፤ ከዚህ አኳያ በሂደቱ የምክክር ኮሚሽኑ የወጣቶች ተገቢ ውክልና መኖሩን ማረጋገጥ እንዳለበት ይናገራል።

ሌላው አዲስ ዓመትንና ወጣትነት በተመለከተ ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረገው ወጣት ሄኖክ ፍቃዱ ነው። የባዩሽ ኮልፌ በጎ አድራጎት ማህበር መሥራች አባል የሆነው ወጣት ሔኖክ እንደሚናገረው፤ አዲስ ዓመት ሲመጣ ምን ያህል የበጎ አድራጎት ሥራዎች ሠርተናል የሚለው ነው የሚያሳስበኝ ይላል።

በአዲሱ ዓመት በተቻለ መጠን ያሉብንን ጉድለቶች በማሻሻል በአዲስ መንፈስ የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ለመሥራት ተዘጋጅተናል የሚለው ሔኖክ፤ <<ለበጎ ሥራ ረፍዶ አያውቅም>> የሚለውን መርህ ቃላችንን መሠረት በማድረግ የበጎነት አድማሳችንን በማስፋት የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት እቅድ እንዳለቸው ይናገራል።

> ወጣቶች መነጋገርና መወያየት አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሀገራዊ ምክክር መልካም ዕድል ሆኖ መጥቷል በዚህ ሂደት በንቃት በመሳተፍ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ መሥራት አለባቸው

በ2016 ዓ.ም በባዩሽ ኮልፌ አማካኝነት በተሰሩ የበጎነት ሥራዎች ጎዳናን ቤታቸው ያደረጉ ከጎዳና የራሳቸውን ቤት የሰሩ ከዚህ ባለፈ ሥራ ፈጥረው ከእርሳቸውን በተጨማሪ ሰራተኛ ቀጥረው ለሌሎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ፣ ለራሳቸው ጥሩ ኑሮ ከመምራት በዘለለ ለሌሎች መትረፍ የቻሉ እንዳሉ የሚናገረው ሔኖክ፤ በዚህም ትልቅ ደስታና እርካታ እንደሚሰማው ይገልጻል።

ወጣት ሆኖ በበጎ አድራጎት ለይ መሳተፍ ምን አይነት ስሜት እንዳለው ሔኖክ ሲናገር፤ በጎነት በቃላት የማይገለጽ ትልቅ ደስታና ዋጋ ያለው ነገር ነው። የተከፉ ፊቶች በደስታ ሲሞሉ ማየት፣ ጠያቂና አጋዥ ለሌላቸው ሰዎች ጊዜ በመስጠትና አብሮ በማሳለፍ የሚገኘው ውስጣዊ እርካታ ትልቅ እንደሆነ ይናገራል።

በዚህ የበጎ አድራጎት ሥራ ውስጥ ብዙ ደስ የሚያሰኙ በዛው ልክ የሚያስከፉ አጋጣሚዎች ይኖራሉ የሚለው ወጣት ሔኖክ፤ ከፍተኛ ሕክምና የሚያስፈልጋቸው በገንዘብ እጥረት ምክንያት ግን ሕክምና መገኘት ተስኗቸው ሞታቸውን የሚጠባበቁ ሰዎች ለበጎነት በተዘረጉ እጆች እርብርብ ተግዘው ለሕክምናቸው የሚያስፈልጋቸው ገንዘብ ተሟልቶ ታክመውና ድነው ደስተኛ ሲሆኑ ማየት ያለው ስሜት በቃላት የማይገለጽ እንደሆነ ይናገራል።

በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ እንደተሰማራ ወጣት በ2017 አዲሱ ዓመት ወጣቶች በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ በንቃት ተሳታፊ እንዲሆኑ መበረታታት እፈልጋለሁ የሚለው ሔኖክ፤ በአጠገባችን ያሉትን ሰዎች ማየት፣ መንገድ ላይ የምናገኛቸውን አቅመ ደካማ ሰዎች መንገድ ማሻገር በራሱ በጎነት ስለሆነ ትንሽ ወይም ትልቅ ሰንል በጎነትን በአካባቢያችን ላሉ ሰዎች በማድረግ መጀመር አለብን ይላል።

በጎነት የሚታይ ፍሬና የሕይወትን ጎተራ የሚሞላ ለግለሰብና ለሀገር የሚተርፍ ተግባር ነው የሚለው ወጣት ሔኖክ፤ በጎነት ከማሰብ በዘለለ፤ አብዝቶ ከመልካም ስራዎች ጎን መሰለፍን፣ ሌሎችን ማገዝ ላይ ማትኮርን ከሰው ምላሽ ሳይጠብቁ ከራስ በላይ ለሌሎች ማድረግን የሚጠይቅ የንፁህ ልብ ክዋኔ እንደመሆኑ ወጣቶች በ2017 ዓ.ም ቀኝ እጃቸውን ለመዘርጋት መዘጋጀት እንዳለባቸው ይናገራል።

ከዚህ በፊት በበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ወጣቶችም በአዲሱ ዓመት የበጎነት አድማሳቸውን በማስፋት በተሻለ ኃይልና ትጋት ዓመቱን በበጎነት ለማሳለፍ መዘጋጀት አለባቸው የሚለው ሔኖክ፤ እንደ ወጣት ትንሽ ትልቅ ሳንል ግዜና ጉልበታችንን ለበጎነት መስጠት አለብን ይላል።

ጎዳና ለወደቁ ዜጎች ማሕበረሰቡ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ማደግ ያለበት ነው የሚለው ወጣት ሔኖክ፤ በኢትዮጵያ ካለውና እርዳታ ከሚያስፈልገው የሰው ቁጥር አንፃር በሀገር ደረጃ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት ጥቂት ናቸው፡፡ ይህ ማለት ተቋማቱ የያዙት የሰው ቁጥር ትንሽ ነው። በየጎዳናው የወደቀው ሰው ደግሞ ብዙ ነውና እንደ ተቋም እንደ ግለሰብ፣ እንደሃይማኖት ተቋም፣ እንደመንግሥት በዚህ አይነት ሥራዎች ላይ በስፋት በመሳተፍ መስራት የግድ እንደሚል ይናገራል።

የተረጂው ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ከማህበረሰቡም ሆነ ከመንግሥት ብሎም ከሕዝቡ ብዙ የሚጠበቅ ሥራ እንዳለ የሚናገረው ሔኖክ፤ ለበጎ ሥራዎች በእኔነት ስሜት መተጋገዝ እና መረዳዳት ከሁሉም የሰው ልጆች የሚጠበቅ የውዴታ ግዴታ እንደሆነም ያስረዳል።

በሌላ በኩል ወጣት ጠብ አጫሪ ከሆኑ ነገሮች እራሱን በማራቅ በተለይ የማህበራዊ ሚዲያን በአግባቡና መልካም ለሆነ ነገር ብቻ በመጠቀም ብሎም በማይመለከተው ነገር ተሳታፊና ሀሳብ ሰጪ ከመሆን እርሱን በመጠበቅ ለሀገሪቱ ሰላም የራሱን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ይናገራል።

ወጣት ሔኖክ እንደሚናገረው፤ በአዲሱ ዓመት ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከመስጠታቸው በተጨማሪ አሁን በአገራችን ላይ ያለው የሰላም እጦት መፍትሔ እንዲያገኝ ወጣቱ ግንባር ቀደም ተዋናይ በመሆን ሚናውን መጫወት ይኖርበታል፡፡ ከነዚህ ሚናዎች መካከል በዋናነት ከበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ በተጓዳኝ በማህበራዊ ሚዲያ ድህረ ገፆች አማካኝነት ሰላም ጠፍቶ ግጭት፣ ልማት ጠፍቶ ጥፋት፣ እድገት ሳይሆን ውድቀት እንዲነግስ ለማድረግ ብሔርን ከብሔር፣ ሐይማኖትን ከሐይማኖት በማጋጨት የሀገርን ሰላም የዜጎችን ወጥቶ መግባት አደጋ ለይ ለመጣል የሚጥሩ ኃይሎችን ሀይ ልንላቸው ይገባል ይላል።

በመጨረሻም ወጣቶቹ ባስተላለፉት መልዕክት አዲሱ ዓመት ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነበት የሕዝቦቿ መተባበርና ፍቅር የጎላበት እንዲሆን ተመኝተው ለመላው የኢትዮጵያ ወጣቶች የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# የማእድን ልማት አበረታች አፈጻጸም- በሲዳማ ክልል

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር አመት መሪ እቅድ የኢኮኖሚው ምሰሶ ተደርገው ከተያዙት አምስት ዘርፎች መካከል የማእድን ዘርፉ ይጠቀሳል። እንደ ሀገር ለውጭ ምንዛሬ ግኝት፣ የገቢ ምርትን ለመተካት፣ ለስራ እድል በአጠቃላይ ለሀገር ምጣኔ ሀብት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ታሳቢ በማድረግም ይህን እምቅ አቅም ለመጠቀም በስፋት እየተሰራ ይገኛል።

ክልሎችም ያላቸውን እምቅ የማእድን ሀብት ለልማት በማዋል ከዘርፉ እነሱም ሀገሪቱም ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተውታል። በዘርፉ በተከናወነው ተግባርም በተለይ ከወርቅ ልማትና ግብይት አኳያ ከህገወጥነት ጋር ተያይዞ ብዙ ፈተናዎች ቢያጋጥሙም በኢንዱስትሪ፣ ኮንስትራክሽን፣ እንዲሁም በጌጣጌጥ ማእድናት ልማት በኩል ለውጦች እየታዩ ናቸው።

ይህ ለውጥ እየታየባቸው ከሚገኙ ክልሎች መካከል የሲዳማ ብሄራዊ ክልል ይጠቀሳል። ክልሉ በተጠናቀቀው የ2016 በጀት አመት በተለያዩ የማእድን አይነቶች ልማትና ግብይት በኩል ለውጦችን እያስመዘገበ ስለመሆኑ የክልሉ የማእድን እና ኢነርጂ ኤጀንሲ ዳይሬክተር አቶ መስፍን መጬካ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ አስታውቀዋል።

ዳይሬክተሩ ኤጀንሲው በ2016 በጀት አመት ለማከናወን ትኩረት ያደረገባቸውንና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ እንዳስታወቁት፤ በክልሉ በበጀት አመቱ በማእድናት ልማትና ጥናት በኩል ከተከናወኑ ተግባሮች አፈጻጸም መረዳት የሚቻለው በማእድን ልማትና ጥናት በኩል በክልሉ ጥሩ እየተሰራ መሆኑን ነው።

በበጀት አመቱ 330 ሜትር ስኩዌር ቦታ ላይ የማእድን ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 378 ሜትር ስኪየር የሆነ ቦታን በጥናቱ ለመሸፈን ተችሏል ሲሉ ጠቅሰው፤ ጥናቱም ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲና ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን መካሄዱን አስታውቀዋል።

በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የወርቅ ማእድን ይገኛል። በእነዚህም አካባቢዎች በተለይ በባህላዊ መንገድ የወርቅ ልማት በማካሄድ የወርቅ ምርቱ ለብሄራዊ ባንክ እንዲቀርብ እየተደረገ ነው። በተጠናቀቀው 2016 በጀት አመትም ይህን ለውጭ ምንዛሬ ግኝት ትልቅ ፋይዳ ያለውን የወርቅ ማእድን በማምረት ላይ ተሰርቷል።

በበጀት አመቱ 15 ኪሎ ግራም ወርቅ በባህላዊ መንገድ በማምረት ለብሄራዊ ባንክ ለማስገባት ታቅዶ እንደነበር ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፣ 13 ነጥብ 7 ኪሎ ግራም ወርቅ በማምረት ለባንኩ ማስገባት መቻሉን አመልክተዋል። አፈጻጸሙም የእቅዱን 91 ነጥብ 7 በመቶ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

እንደ ሀገር የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካትና ምርቶችን ከውጭ ለማስመጣት ይወጣ የነበረውን የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረት እየተከናወነ ያለው ተግባር በሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥትም በስፋት እየተሰራበት ይገኛል። በዚህም በኩል ክልሉ በተጠናቀቀው በጀት አመት 2500 ቶን ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውሉ ማእድናት ለፋብሪካዎች ለማቅረብ አቅዶ እንደነበር አቶ መስፍን ጠቅሰው፣ በእዚህም ከእቅድ በላይ 3100 ቶን ማእድናትን ለፋብሪካዎች ማቅረብ መቻሉን ነው ያመለከቱት።

አቶ መስፍን እንዳስታወቁት፤ ኤጀንሲው በግንባታ ግብአት ማእድናት አቅርቦት ላይ በስፋት እየሰራ ይገኛል። በበጀት አመቱ አራት ሚሊዮን ሜትር ኩብ የግንባታ ማእድናትን ለገበያ ለማቅረብ አቅዶ 4ሚሊዮን 280 ሺ 500 ሜትር ኪዩብ አቅርቧል።

ክልሉ በማእድን ልማት ከሚያከናውናቸው ተግባሮች መካከል የጌጣ ጌጥ ማእድናት ማምረት ሥራ አንዱ ነው። እነዚህን በሀገር ውስጥም በዓለም አቀፍ ደረጃም በስፋት የሚፈለጉትን የጌጣጌጥ ማእድናት ለማምረቱ ሥራ ትኩረት ሰጥቷል። በ2016 በጀት አመቱም 40 ቶን የጌጣ ጌጥ ማእድናትን ለማምረት ታቅዶ 73 ቶን ማምረት ተችሏል።

የማእድን ልማት ሥራዎች ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ማእድናትን በማምረት ለገበያ ከማቅረብ በተጓዳኝ፣ በዘርፉ የሚሰማሩ ባለሀብቶችን በመሳብ እንዲሁም ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠርም ይታወቃሉ።

በሲዳማ ክልል በበጀት አመቱ በማእድን ልማት በተከናወነው ተግባር ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር የተቻለበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል። በክልሉ በበጀት አመቱ ለ6000 ሰዎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ5860 ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር እንደተቻለ አቶ መስፍን ጠቅሰው፤ አፈጻጸሙም የእቅዱን 97 ነጥብ 6 በመቶ መሆኑን አመልክተዋል።



**አቶ መስፍን መጬካ፤**

እነዚህን አፈጻጸሞች ለማስመዘገብ የተከናወኑ ተግባሮችን እንዲሁም በቀጣይ ሊከናወኑ የተያዙ ሥራዎችንም አቶ መስፍን አያይዘው ገልጸዋል። በበጀት አመቱ ጥናቶች የተደረጉባቸው አካባቢዎች የአሮሬሳና አኮ ወረዳዎች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በእነዚህ አካባቢዎች በጥናት የተለዩት ማእድናትም የኮንስትራክሽን ማጠናቀቂያ ግብአቶች የሚባሉት መሆናቸውን ገልጸዋል። በጥናቶቹም ግራናይትና እምነበረድ መገኘታቸውን በላቦራቶሪ ውጤት ጭምር ማረጋገጥ መቻሉን አስታውቀዋል። በቀጣይም ተመሳሳይ ሥራ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

እንደ ሀገርም ካለው የማእድን ሀብት አኳያ ሲታይ በጥናት የተለየው በጣም ውስን ነው ይላሉ። ይህን ማእድን ለማጥናትም እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመው፤ በኛም ክልል በጆኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት በኩል የወርቅ ጥናት ተካሂዷል ሲሉ ገልጸዋል።

ኢንስቲትዩቱ በጂምስቶን ላይ ያጠናልናል፤ እኛም በራስ ሀይል ጥናት እያደረግን ነው ሲሉ ተናግረው፣ የኢንዱስትሪና የኮንስትራክሽን ግብአት በሚሆኑ ማእድናት ላይም እንዲሁ ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ለማጥናት መታቀዱንም አመልክተዋል።

በባህላዊ መንገድ በስፋት እየተካሄደ ያለውን የወርቅ ልማት ለማዘመንና ልማቱ በኩባንያ ደረጃም እንዲካሄድ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ማህበራት እና ባለሀብቶች አብረው እንዲሰሩ እንዲሁም ኩባንያዎች በራሳቸው ልማቱን እንዲያካሂዱ ለማደረግ እየተሰራ ነው። ባለሀብቶችም የወርቅ ማጠቢያ ማሽንና ኤክስካቫተር ይዘው ገብተው መሥራት ጀምረዋል። ሌሎች በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የተሰጣቸው ሁለት ኩባንያዎች ወርቅ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ጽንስ ወርቅ ላይ ጥናት እያደረጉ ናቸው።

ከወርቅ ልማትና ግብይት አኳያ በተለያዩ ወርቅ አምራች ክልሎች ህገወጥነት መንሰራፋቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። መንግሥት ይህን ህገወጥነት ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል አቋቁሞ እየሰራ መሆኑም ይታወቃል። ይህን ተከትሎም በርካታ የውጭ ዜጎች ጭምር በእዚህ ህገወጥ ተግባር ተሰማርተው በመገኘታቸው እርምጃ እንደተወሰደባቸው ይታወሳል። ለእዚህ ህገወጥነት መንሰራፋት አንዱ ምክንያት ማእድኑ በሚለማበት አካባቢ ያለው የጸጥታ ችግር መሆኑ ይጠቀሳል።

በሲዳማ ክልል የጸጥታ ችግር ካለመኖሩ ጋር በተያያዘ ህገወጥነቱ ያን ያህል የሰፋ እንዳልሆነ አቶ መስፍን ገልጸዋል። በተወሰነ መጠን የመቀነስ ሁኔታ እንደሚኖር ይገመታል። ያንን ለማጥፋት አልሚዎቹ የየእለቱን ምርታቸውን እንዲመዘገቡ ይደረጋል። ለእዚህም በየሳይቱ መዝገብ ተዘጋጅቷል ሲሉም ገልጸዋል።

መንግሥት የውጭ ምንዛሬ ግብይቱን ከጥቁር ገበያው ጋር ስላቀራረበው ህገወጥነቱ በራሱ ጊዜ እየቀነሰ ይሄዳል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ እኛም ከጸጥታ ኃይሎችና ከወረዳ ማእድን ግብረ ኃይሎች ጋር ተባብረን የየእለቱ ምርት እንዲመዘገብ የቁጥጥር ስራ እናካሂዳለን። ይህንንም ህገወጥነት መከላከል የሚያስችል ንቅናቄ በማድረግ አጠናክረን እንቀጥላለን። በእዚህም ማህበረሰቡ ራሱ እንዲሳተፍ እናደርጋለን ብለዋል።

የገቢ ምርቶች መተካት ላይ ክልሉ በተጠናቀቀው በጀት አመት ጥሩ አፈጻጸም አሳይቷል። ለአፈጻጸሙ ውጤታማ መሆን ገበያ ላይ የተሠራው ሥራ አስተዋጽኦ ማድረጉ ተገልጿል።

በክልሉ በኢንዱስትሪ ግብአት ምርትነት በዋናነት እየተሰራበት ያለው የሴራሚክ ግብአት በሆነው ታልክ ላይ ነው ሲሉ አቶ መስፍን አስታውቀዋል። ይህ ግብአት በሀዋሳ ሴራሚክ ፋብሪካ እንዲሁም ዱከም አካባቢ በተቋቋሙ የሴራሚክ ፋብሪካዎች በብዛት ይፈለጋል ሲሉም ገልጸው፤ እንደ ኳርትዝ እና ፊልድስፓር ያሉ የኢንዱስትሪ ግብአት ማእድናትም በክልሉ እንደሚመረቱ ተናግረዋል።

ዘንድሮ ለፋብሪካዎች በብዛት የቀረበው ታልክ የተሰኘው




> **ክልሉ በተጠናቀቀው በጀት አመት 2500 ቶን ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውሉ ማእድናት ለፋብሪካዎች ለማቅረብ አቅዶ፣ከእቅድ በላይ 3100 ቶን ማእድናትን ለፋብሪካዎች ማቅረብ ችሏል**

ማእድን መሆኑን አመልክተው፣ ይህ ማእድን በአሁኑ ወቅት ፋብሪካዎች በስፋት እንደሚፈልግና ማእድኑም በስፋት እንደሚገኝ ገልጸዋል። በክልሉ ጥራቱን የጠበቀ የታልክ ማእድን እንዳለም ነው የተናገሩት፡

አቶ መስፍን እንዳስታወቁት፤ በዚህ የሴራሚክ ግብአት አምራችነት ከሰባት እስከ ስምንት የሚደርሱ ማህበራት ተሰማርተዋል፤ የማህበራቱ ቁጥር በየአመቱ እየጨመረ ነው። ፊት ኢንዱስትሪዎች ካለመስፋፋታቸው ጋር በተያያዘ የገበያ ችግር ይታይ ነበር። አሁን ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ መምጣቸውን ተከትሎ ማእድኑን የሚያመርቱ ማህበራት ቁጥርም እየጨመረ ነው። ወጣቶችም በማህበር በመደራጀት ማእድኑን እያወጡ ለገበያ በማቅረብ ሥራ ላይ በስፋት እየተሰማሩ ናቸው።

በኢንዱስትሪ ማእድናት ላይ የሚካሄደው ልማት ይቀጥላል። የመንግሥት አንዱ የልማት አቅጣጫ ኢንዱስትሪ ማስፋፋት ላይ ያተኮረ እንደመሆኑ፤ በተለይ የገቢ ምርትን በመተካት ላይ በተጠናከረ መልኩ ይሰራል። ክልሉም በእዚሁ ልክ በእነዚህ የኢንዱስትሪ ግብአት ማእድናት ልማት ላይ መሥራቱን ይቀጥላል። የማእድን ልማቱ ለወጣቶች የሥራ እድል በመክፈት በኩል ባለው ፋይዳም ትኩረት ተሰጥቶታል።

እሳቸው እንዳሉት፤በግንባታ ግብአት እንደ ግራናይት ባሉት ማእድናት ላይ ያተኩራል። በክልሉ አራት ባለሀብቶች በግራናይት ማእድን ልማት ለመሰማራት እየተንቀሳቀሱ ናቸው። ባለሀብቶቹ የድንጋይ መቁረጫ ማሽን ለመግዛት አዘዋል። ማሽኑ ከመጣና ወደ ስራ ከገባ ግራናይትም ወደ ሥራ ይገባል ተብሎ እንዲሚታሰብ አቶ መስፍን አመልክተዋል።

ሌላው በክልሉ ጥሩ አፈጻጸም የታየው በጌጣጌጥ ማእድናት ልማት ላይ እንደመሆኑ ልማቱ በቀጣይም የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል። በክልሉ እየለማ ያለው ፉታይል የሚባል የጌጣጌጥ ማእድን ሲሆን። በእዚህ ልማት ላይም ወደ አራት የሚሆኑ የወጣቶች ማህበራት ተሰማርተዋል። ማእድኑ እሴት ሳይጨመርበት ወደ ቻይና እየተላከ ይገኛል። ማእድኑ በክልሉ አኮ ወረዳ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ የሚመረተውም በባህላዊ መንገድ ነው፤ አምራቾቹ ኤክስካቫተር ተከራይተው የሚያመርቱበት ሁኔታም አለ።

ይህ የጌጣጌጥ ማእድን እንደ ኦፓል የከበረ የሚባል አይደለም ያሉት አቶ መስፍን፣ ከፊል የከበረ ጌጣጌጥ የሚባል ነው ይላሉ። በእዚህም ላይ ከሌሎች ክልሎች ልምድ በመውሰድ እሴት በመጨመር ለገበያ ለማቅረብ ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር ጥረት እንደሚደረግ ጠቁመዋል።

ለማእድን ምርቶች ገበያ በማፈላለግ በኩል ምን ያህል እየተሰራ ነው የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ መስፍን፤ ‹‹ቀደም ሲል የኢንዱስትሪ ግብአት ማእድናት ምርት ገበያ ለማግኘት ችግር ነበር፤ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ያከናወናቸውን የማስተዋወቅ ስራዎች እየተመለከቱ አምራቾች አሁን ምርቱን ፍለጋ እየመጡ ናቸው፤ ገበያውም በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል›› ሲሉ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

መንግሥት የመዋቅር ለውጥ ጭምር በማድረግ ለማእድን ዘርፉ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል። የዘርፉን እምቅ አቅም ማሳየት ያስቻሉ፣ አምራቾችንና ኢንዱስትሪዎችን ያስተሳሰሩ ዓለም አቀፍ ኢግዚቢሽኖችም ባለፉት አመታት ተካሂደዋል።

ክልሎችም በዘርፉ ያላቸውን እምቅ አቅም ታሳቢ ባደረገ መልኩ መዋቅሮችን ፈጥረው በልማትና ግብይቱ ላይ መስራታቸውን ተያይዘውታል። ይህን ተከትሎም በክልሎች ብዙ ለውጦች እየታዩ ናቸው። በተለይ በድንጋይ ከሰል፣ በሴራሚክ ግብአት ማእድናት ምርት በኩል ለውጦች መመዝገብ ጀምረዋል።

በሲዳማ ክልልም በማእድን ልማት በኩል እየታየ ያለው ለውጥም ከዚሁ አኳያ ሊታይ ይችላል። አቶ መስፍንም ይህንኑ ነው ያሉት። በተጠናቀቀው በጀት አመት በአብዛኞቹ ማእድናት ልማት ስራዎች ላይ ከእቅድ በላይ አፈጻጸም መመዝገቡም ለውጡ እየጨመረ መምጣት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል አመልክተዋል። የማእድን ጥናት ረጅም ጊዜን የሚወስድ ሆኖ እንጂ በጥናት በኩል እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮች ሲጠናቀቁ በክልሉ በቀጣይም በዘርፉ ለውጦች እንደሚመዘገቡ ይጠበቃል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ በቀጣይም ከእስከ አሁኑም የሰፋ አቅድ በመያዝ በማእድን ዘርፉ ላይ ይሰራል። በክልሉ በጸጥታው በኩል ያለውን አስተማማኝ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በዘርፉ ላይ በስፋት የሚሰራ ይሆናል።

በክልሉ በተካሄደ ጥናት በመዳብ/ኮፐር/፣ በታንታለምና በመሳሰሉት ማእድናት ላይ ጥናት እየተካሄደ ይገኛል ሲሉም ጠቁመው፣ በርካታ ባለሀብቶችም በክልሉ በጸጥታው በኩል ያለውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም ወደ ክልሉ መጥተው በማእድናት ላይ ጥናቶችን እያደረጉ መሆናቸውን አስታውቀዋል። እነዚህ ጥናቶች ቢጠናቀቁ እንደ ክልል ብቻም ሳይሆን እንደ ሀገርም አፈጻጸሙ ከፍ ይላል የሚል እምነት እንዳላቸው አቶ መስፍን አስታውቀዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## መስታወት አስተዋዋቂው ገዴ በመንገዴ

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)**

በየዓመቱ የበዓልን መምጣት ተከትሎ ከቅርብ ጎረቤቶቼ ጋር በመሆን ሙክት ልንገዛ በምሄድበት ሰሞን የተወዳጀሁት በግ ነጋዴ ወዳጅ አለኝ። በኑሮ ውድነቱ ሁሉም ቤት ያፈራውን ቀምሶ የሚውልበት ክፉ ቀን ሳይመጣ በፊት ማለቴ ነው...። ገበያ ደርሼ ይሄን ወዳጄን ሳላይ አልመለስም በሚል የራስ ሙግት ወደ በግ ተራ አቀናሁ።

በገበያ ሳልፍ.. አንድ የመስታወት ማስታወቂያ አይቼ ፈገግኩ። በተለያየ ቅርጽ የተሰሩ የተለያየ መጠን ያላቸውን መስታወት የሚሸጥ ሰው በእጁ አንድ መስታወት ይዞ ወረሩን በመስታወቱ ውስጥ እያጤነ..‹ውበት የሚጨምር የቤቶ ግርማ ሞገስ..እኔ ነኝ እንዴ ብለው በራሶ ግራ እስኪጋቡ ወዘናዎን የሚመልስ መስታወት..እኔ ዘንድ ብቻ ይገኛል›

በሰውዬው ተስቤ ባለሁበት ቆምኩ..ጥቂት ሰዎች ሳቅ ባረበበበት ገጽ ከበውታል። አንዳንድ መንገደኞች ወዳለበት ይተማሉ..። ከስንት አንድ የሚሆኑት በማስታወቂያው ተታለው (ሌላ ምን ይሆናል?) ከተቀመጠበት መስታወቱን በማንሳት የተባለውን ለማረጋገጥ ራቅ ቀረብ እያደረጉ ራሳቸውን ሲመለከቱ አየሁ። እብድ ቀን አይመሽም ትል ነበር እናቴ..እብድ ቀን የቱን ዓይነት እንደሆነ ግራ እንደገባኝ አደኩ። አሁን ሲመስለኝ እብድ ቀን ይሄ ዓይነቱ ቀን ይመስለኛል። ይሄ ቀን እብድ ካልሆነ ከዚህ የተለየ እብድ መሳይ ቀን ከወዴት ይመጣል?

እኔም ወደ ሰውዬው አፈገፈግኩ። አንድ እብድ በገዛ ሃሳቡ አብዶ ብዙ ጤነኞችን ወደ እብድነት ሲቀይር አስባለሁ። ከነዛ እብዶች መሀል አንዱን ሆኜ ወደዛ ሰው መጠጋቴ እንደከበቡት ሰዎች ገጼ ፈገግታን ጻነሰ። እውነት ቢሆንስ ስል በሥርዓት ከተደረደሩት መስታወቶች አንዱን አንስቼ መልኬን መቃኘት ያዝኩ..ከነባሩ መልኬ ምንም የተለወጠ ነገር አላስተዋልኩም። ለሰላሳ ሁለት ዓመታት የማውቀው ራሴ ነኝ። ቤታችን ግድግዳ ላይ በተሰቀለው ከጀርባው አንዲት የቻይና ሞዴልን በለጠፈው መስታወት የማውቀው መልኬ ነው። እንደተሞኘሁ ያወኩት ይሄን ጊዜ ነው።

ወደሰውዬው አሰገግኩ..ጮሌነትና አራዳነት ወጣት ይሁን ጎልማሳ እድሜውን በደበቀ ፊቱ ላይ አስተዋልኩ። ከቅንድቡ ከፍ ብሎ ግራ ግንባሩ ላይ ደም ስር ተጋድሟል.. ደምስሩን አጤንኩት ቀስተኛ እንቅስቃሴ ያደርጋል። ወደሽፋሽፍቱ አየሁ..ቢቆጠሩ አስር የሚሆኑ ብቻ ናቸው።

የምገዛው መስሎት ‹አሪፍ መስታወት ነው የመረጥከው.. በጥሩ ዋጋ እሸጥልሃለሁ። በአሁኑ ሰዓት በምድር ላይ ያለ ብቸኛው የስጦታ እቃ ነው...ፍቅረኛ ካለችህ..ከሌለህም ለምትመጣው ይሆንሃል..እንዳያመልጥህ› ሲል ረጅም ወግ አወጋ።

መዳፌን አየሁት..ከሰላምታ በቀር ሰው አጠናፍሮ አያውቅም፣ ይሄን ሰው በማጠናፈር የመጀመሪያው ታሪከኛ መዳፍ ላደርገው አሰብኩ። ፊቱ ላይ የአምስት ጣቴን ሰንበር ከመዳፌ ሙዳ ጭረት ጋር መተው አሰኝቶኝ ነበር። ለአንድ ጊዜ በመጣ እልኸኝነት ፊቱ ላይ ብዘምትበት..ጮሌነቱን በቡጢ በአደባባይ ባስንቅበት ፈለኩ። እንዲህ በሽቁ እመለሳለሁ እንጂ ያበሸቀኝን ሰው ላይ እልሄን ተወጥቼ አላውቅም። ፈሪ ሆኜ እንዳልሆነ አውቃለሁ..በእውነቱ ለክብሩ የሚሟገት ብርቱ ሰው ነኝ። በኋላን በአሁን ፊት አስቀምጬ ነገን እማልዳለሁ ያኔ እረጋጋለሁ..

እንዴት ወደዚህ ሰው መጣሁ? እብድ ቀን አብዶ የሚያሳብድ ይሆን? እናቴ ዳግም እቅፏ ውስጥ አስቀምጣ ብትነግረኝ..። ባልገቡን የሕይወት ፈር ስር ነን..እየጠየቅን እስከነገ እንድንሄድ በሆነ ሰው መሆን ውስጥ..

አየሁት! አፊ ግንዱን ሲያብስ አገኘሁት። ፊቱ ቅድም በሌለ ላብ አቸፍችፏል። ስሩ መቆሜ አንዳች ልፈጥርበት እንደሆነ ገብቶት ያላበ መሰለኝ። ባይመስለኝም በዛ ማላዘን ላብ አይደለም ሌላም ነገር ሲያንሰው ነው። እያሳዘነኝ መጣ.. ከኋላው አንዳች ታሪክ አነበብኩ። አልሸጥ ብሎት..ሊከስር እንደሆነ ሲያውቅ አፍረቱን ከልሎ በእብድ መላ ሰው ፊት የቆመ መሰለኝ.. ፊቴን መስታወቱን እንደማልፈልግ በሚናገር ሁኔታ ወደነበረበት ብመልሰው ገበያውን የምዘጋበት መስሎ ታየኝ። ወትሮስ ሃሳቤ ምን ሆነና እንደዚህ አሰብኩ? ቢቻለኝ ግብግብ ፈጥሬ አንተ ሌባ ወራዳ ብዬ እሪ ብዬ ላሲዘው እንዳላሰብኩ ደርሶ አዛኝ መሆኔ ለራሴም ገረመኝ።

በውሸቱ ተታለው ብዙ ሰዎች እየገዙት ሄዱ። እኔና እሱ ብቻችንን መቅረታችንን ሳውቅ አንድ ሁለት ጥያቄዎችን ልጠይቀው ሰሰናዳ..

‹ምነው አልተመቸህም እንዴ? ስለእቃው ጥራት እኔ ከምነግርህ በላይ ያየሃቸው ደንበኞቼ ምስክሮች ናቸው። አሁን ፊቴ ቆመው ሲገዙኝ ያየሃቸው የቆዩ የመስታወት ደንበኞች ናቸው። በሳምንት ሁለት ጊዜ ይገዙኛል› ሲል ቀላመደ። በሳምንት ሁለት ጊዜ? አልኩ በብሽቀት ለራሴ። ቆይ ምኔ ሞኝ ይመስላል? ምኔ ላይ ቂልነትን አየብኝ? የተደበቀ ሞኝነቴን ፍለጋ ራሴን ከእግር እስከራሴ ቃኘሁት.. ራስን በዚያ መንገድ መፈተሽ..በድርጊቴ ሳቄ መጣ። በድጋሚ በመስታወቱ ውስጥ ራሴን በጥንቃቄ ፈተሽኩት..በትንሹ ከታጠፈ የሸሚዜ ኮሊታ በቀር ክፉ አላገኘሁም። ምናባቱ ሆኖ ነው ታዲያ እንደሞኝ ደንበኞቹ ሊያሞኝ የተነሳው ስል አፈጠጥኩ። በሸሚዝ ላይ ኮት ነውር ይሆን?

ዓይኖቼን እንከን ወደማያጣው እግሮቼ ሰደድኩ.. ጫማዬ ከአንድ ጎን ተበልቶ ተረከዜን ገንድሶ፣ ሚዛኔን ወደአንድ ጎን አንሸራቶ ጅላንፎ አስመስሎኛል። ጫማ ገዝቼ በሳምንቱ ለምን እንደዛ እንደሚሆንብኝ ለብዙ ዘመን ያልተመለሰ ጥያቄ አለኝ። ዓለም የእግር ባለጅ ባለማኖሯ እንደትልቅ እንከን እቆጥርባታለሁ። እንደ ብረት ሙያተኛ እግርም ቀጥቃጭ ቢኖረው እላለሁ። በምድር ላይ ጫማህን ፍታ እንደሚል ቀልድ የማልወደው የለም። ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ካልሲዎቼ እንዳለ ቀዳዳዎች ናቸው። ተቀዶ አይቶት ይሆን..? ወይስ በተረከዜ መበላት እንደቂላቂል ቆጥሮኝ?

ኧረ እንደው ልቤ ድፈርና ዛሬ ልኩን አሳየው ይለኛል ውስጤ..ተው አይሆንም የሌለበት ወኔ ናፈቀኝ። ተያይዘን ለገላጋይ የምናስቸግርበት ትዕይንት እየመጣ ይሄድብኛል። ‹በሳምንት ሁለት ጊዜ ይገዙኛል› ያለኝ ቧልቱ አልረሳ ብሎ ለቡጢ ይተናነቀኛል። ከልጅነቴ ጀምሮ መልኬን እያየሁበት ያደኩት የእናቴ ወዛም ዘኒት ቅባትና አደስ እያሟለጨኝ ልጅነቴን የሰዋሁበት በኋላም ከእሷ ወደእኔ ተላልፎ በቅርስነት ሊመዘገብ ጥቂት የቀረው የቤታችን እድሜ ጠገብ መስታወት ስንቱን ትውልድን የኳለውና ለቁም ነገር ያበቃው ለብቻው አይደል? ዛሬ በዚህ ሰው የሀሰት ትርክት ውለታው መበላቱ አናደደኝ። እብለቱ እያበሳጨኝ መጣ።

‹ለመሆኑ ይሄን በድህነት የሚማቅቅ ሕዝብ የማደናገሪያ ጥበብ ከየት አገኘኸው? ስል ጠየኩት።

አልደበቀኝም..አይነግረኝም ብዬ ስሰጋ እንደ ግምቴ እቅጩን ነገረኝ። ‹ሕይወት ናት እንኳ ስትል የሰጠችኝ› ሲል ወደልፍለፋው ተመለሰ።

ባልገባው ፊት ‹እንዴት ማለት? በማለት በተራዬ ከልፍለፋው አስተጓጎልኩት።

‹የእኛ ሰው አስቸጋሪ ፍጡር ነው እውነት ብትነግረው አያምንህም። ውሸት ስትነግረው ግን እንዳየኸው በወረፋ ተረባርቦ ነው የሚቀበልህ። እንዳየኸው ይሄ መስታወት ውበት የሚጨምር ሆኖ አይደለም እውነቱን በውሸት ቀይሬ በመናገሬ ያመጣሁት ነው። ሰው እውነትን ካልመረመረ ውሸታሞች አንድ ሲደመር አንድ ሶስት ነው ብለው ይመጡበታል። አሊያም በበሬ ወለደ መሞት ለማይፈልጉ እነሆ የሞት መድኃኒት ስትል ሰናፍጭና ዳማከይሴን ቀላቅለህ በቀን ሶስቴ በሚል ትዕዛዝ እንደባሕል ሐኪም ከጥሩ ማስታወቂያ ጋር ውድ ዋጋ አውጥተህለት ጎዳና ላይ ትሰየማለህ..አትጠራጠር ያምንሀል› ሲለኝ እኔም አምኜው በሚቀጥለው ቀን ለዚህ ውሸት ራሴን በማሰናዳት ነበር።

ምንም ሳልለው ላነሳሁት መስታወት የሚገባውን ከፍዬ ወደበግ ነጋዴ ወዳጄ ተሰደድኩ። መንገድ ላይ ነበር ከእሱ የባሰኩ እብድ እንደሆንኩ የተገለጠልኝ..ውሸት እንደሆነ እያወኩና እየነገረኝ መግዛቴን ሳውቅ።

እብድ ቀን ላይ አይደለሁ..! መልኬን ከቀየረው ብዬ መንገድ ላይ ፊቱን በመስታወቱ ውስጥ አጤንኩት..። ከኋላዬ በሁኔታዬ ተገርማ ይመስለኛል አንዲት መልከ መልካም ፎቶ እንደሚነሳ ሰው ፈገግ ብላ ቆማ አየሁ...

እያወጋን ሄድን..ከሶስት ወር ቆይታ በኋላ ሚስቴ ላደርጋት ቀለበት ያሰርኩላት መሆኔን ማን ያምናል?

# ዓስም አቀፍ

## ጀርመን የድንበር ጥበቃዋን እንደምታጠናክር አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፈው ነሐሴ ወር ጀርመን በስሎይንጋን ከተማ የደረሰውና ለሦስት ሰዎች ህልፈት ምክንያት የነበረውን የስለት ጥቃት ተከትሎ የድንበር ፍተሻና ጥበቃዋን ልታጠናክር ነው።

ጥቃቱን እንዳደረሰ የተጠረጠረ ግለሰብ ሶሪያዊ ዜግነት ያለው ሲሆን፤ ያቀረበው የጥገኝነት ጥያቄ ወድቅ ተደርጎ ከጀርመን ተጠርዞ እየወጣ ነበር ተብሏል። በዚህም ሳቢያ የጀርመን መንግሥት የድንበር ጥበቃውን እንዲያጠናክር ጫና ሲደረግበት ነበር። አይ ኤስ የተባለው ቡድን የዚህን ጥቃት ኃላፊነት ወስዷል።

ከአምስት ቀናት በኋላ ሥራ ላይ የሚውለው እና ለስድስት ወራት የሚቆየው አዲሱ የድንበር ጥበቃ በአካባቢያዊ ምርጫ ትልቅ ተቀባይነት ያገኘ ነው።

የጀርመን የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ናንሲ ፋኢሰር መንግሥት መደበኛ ላልሆኑ ስደተኞች “ጠንካራ መስመር” ያስቀምጣል ያሉ ሲሆን፤ የሚስፋፋው ፍተሻ የእስላማዊ ጽንፈኝነትን እና ድንበር ተሻግረው የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ “ሕዝባችንን ከዚህ ስጋት ለመከላከል ባለን አቅም ሁሉንም ነገር እናደርጋለን” ሲሉም አክለዋል።

ጀርመን በምሥራቅ እና ደቡብ ከሚያዋስኗት ፖላንድ፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ስዊዘርላንድ እና ኦስትሪያ ድንበሮች ላይ የባቡር እና የየብስ ፍተሻ ታደርጋለች።

በአዲሱ አሰራር መሠረት በሁሉም ደንበሮች ላይ ፍተሻ ይጀመራል።

ሆኖም ይህ እርምጃ ከደህንነት ይልቅ ፖለቲካ የተጫነው ነው የሚል ትችት እያስተናገደ ነው።

ከናዚ በኋላ በምሥራቃዊ የሀገሪቱ ክፍል ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው የጀርመን የቀኝ አክራሪ ፓርቲ ስደተኞችን የመቀነስ ዕቅዱ ላይ በሚገባ አልሠራም በሚል ከፍተኛ ጫና እየደረሰበት ነው።


ጀርመን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአንጻራዊነት ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ጥገኝነት ጠያቂ በሀገሪቱ እንዲኖር ፍቃድ ሰጥቷል።

ጀርመን ከአውሮፓውያኑ 2015 እስከ 2016 ባለው ጊዜ እንደ ሶሪያ ካሉ አገራት ከ1 ሚሊዮን በላይ ስደተኞችን የተቀበለች ሲሆን፤ የዩክሬን ጦርነት በ2022 ሲቀሰቀስ ደግሞ 1.2 ሚሊዮን የዩክሬን ዜጎችን ተቀብላለች።

ኤኤፍዲ የተሰኘው ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ስደተኞችን የሚመለከት አዲስ እቅድ ያወጣ ሲሆን፤ በዚህ ሳምንት መጨረሻ በሚደረገው ምርጫ የተሻለ አፈጻጸም እንደሚኖረው ተገምቷል።

ሆኖም የቀድሞ የጀርመን መራሂተ መንግሥት አንጌላ ሜርክል ፓርቲ መስፈርቱን የሚያሟሉ ጨምሮ ሁሉንም ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ድንበር የመውሰድ ዕቅድ አቅርቧል። ከዚያም ከድንበር ተነስተው ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገራት እንዲሻገሩ ማድረግ የዕቅዱ አካል ነው።

ሆኖም ይህ ዕቅድ ከኦስትሪያ ተቃውሞ




ገጥሞታል። የኦስትሪያ የአገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትር ቢልድ ለተባለው መገናኛ ብዙኀን ትናንት ሰኞ በሰጡት አስተያየት፤ አገራቸው በጀርመን ተቀባይነት ያጣን ስደተኛ እንደማትቀበል ተናግረዋል።

“በዚህ ጉዳይ የሚለወጥ አቋም የለም” ሲሉ አክለዋል። ባለፈው ነሐሴ ከደረሰው የስለት ጥቃት በኋላ የጀርመን መንግሥት ስደተኞች ላይ ልዩ ልዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ናይጄሪያ ዜጎቿ “የተፀለየበት” እየተባለ የሚሸጥ ውሃ እንዳይጠቀሙ አስጠነቀቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የናይጄሪያ መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን “የተፀለየበት” ተብለው የሚሸጡ እና በናይጄሪያዊው የቴሌቪዥን ወንጌል ሰባኪ፤ ጀርማያ ፋፌይን ቤተ እምነት በኩል የሚቀርቡን ምርቶች ከመግዛት እንዲቆጠቡ ዜጎችን አስጠነቀቀ።

ባለሥልጣኑ “የተፀለየበት ውሃ” እና “የዮርዳኖስ ወንዝ ውሃ” እየተባሉ ታሽገው የሚሸጡ ምርቶች መካን የሆኑ ሴቶች እንዲወልዱ ያደርጋሉ በሚል “በሐሰት” እንደሚሸጡ ገልጿል።

መግለጫው አክሎም ምንም እንኳ የባለስልጣኑ ፈቃድ ባያገኝም ወንጌል ሰባኪው ጀርማያ ፋፌይን የሚመራው ‘ክራይስት ሜርሲላንድ ዴሊቨረንስ ሚኒስትሪ’ ምርቶቹን እየሸጠ እንደሚገኝ ገልጿል።

ቤተ እምነቱ በበኩሉ “ሕግን አክብሮ የሚሰራ” መሆኑን በመግለጽ የተቋሙን መግለጫ “መንፈሳዊ ነገሮችን ባላቸው መንፈሳዊ እምነት” ልክ እንደሚጠቀም ገልጿል።

እሁድ እለት በተጋራ መግለጫ፣ ክራይስት ሜርሲላንድ ዴሊቨረንስ ሚኒስትሪ በናይጄሪያ ሕግ መሠረት እንደሚንቀሳቀስ ገልጾ፣ ይህም ያለምንም ጣልቃ ገብነት የእምነት ነጻነትን ይፈቅዳል ብሏል።

የመድኃኒት ቁጥጥር ባለስልጣኑ ምርቶቹ ላይ ምርመራ የጀመረው ከዜጎች ቅሬታ ከደረሰው በኋላ መሆኑን ገልጿል።

አክሎም ምርቶቹ የቁጥጥር ባለስልጣኑን ፈቃድ ያላገኙ እንዲሁም የጀርማያ ቤተ እምነትም “በምርመራው ላይ ለመተባበር ዳተኛ የሆነበት” መሆኑን አስታውቋል።

ቤተ እምነቱ በዩቲዩብ ያሉት በሺህዎች የሚቆጠሩ ተከታዮች፣ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የባለስልጣኑን ክስ ያስተባብላሉ።

አክለውም ቤተ እምነቱ ለባለስልጣኑ በደብዳቤ ምላሽ መስጠቱንም ገልጿል።

ጀርማያ በናይጄሪያ የተአምራት እና የፈውስ አገልግሎት በመስጠት በርካታ ተከታዮችን አፍርቷል።

ቢሊየነር እንደሆነ የሚናገረው ሰባኪው፣ በቅንጡ አኗኗሩ የተነሳ ትችቶች ይቀርቡበታል።

በናይጄሪያ የተጸለየባቸው እየተባሉ የሚሸጡ የተለያዩ ምርቶችን ማግኘት የተለመደ ነው።

ከዚህ ቀደም ቲቢ ጆሽዋ የመፈወስ አቅም አላቸው እየተባሉ የሚሸጡ “የተፀለየበት ውሃ” ነበረው።

የቢቢሲ ምርመራ ዘገባ ቲቢ ጆሽዋ ታምመው ወደ ቤተ እምነቱ ይመጡ የነበሩ ምዕመናን መድኃኒታቸውን እንዲያቋርጡ ያበረታታ እንደነበር ይፋ አድርጓል።

በጎን ግን በምስጢር የተደራጁ የፋርማሲ ባለሙያዎች የታዘዘውን መድኃኒት “ይፈውሳሉ” ከተባሉ የፍራፍሬ ጭማቂዎች እና ውሃዎች ጋር በመቀላቀል ለተከታዮቹ ይሰጥ ነበር ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ለብዙዎች ሕይወት የተስፋ ብርሃን የፈነጠቀው ምግባረ ሰናይ ተቋም

**አንተነህ ቸሬ**

ዓለማችን በተራቀቁ የቴክኖሎጂ ውጤቶችና ኅብረተሰባዊ መስተጋብሮች ምክንያት አንድ ትንሽ መንደር ሆናለች በምትባልበት በዚህ ዘመን፣ መከራዋና ሰቆቃዋም በዚያው ልክ እየበዛ ነው። በየቦታው የሚፈጠሩ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሕዝቧን ለስቃይና መከራ እየዳረጉ ቀጥለዋል። እነዚህ ችግሮች ደግሞ በርካታ ማኅበራዊ ቀውሶችን አስከትለዋል።

‹‹ቅንነት ሞተ፣ መተዛዘን ጠፋ …›› የሚሉ ድምጾች ደጋግመው ይደመጣሉ። በተለይም የኢትዮጵያውያን መገለጫ ተደርገው የሚቆጠሩት ባህርያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸሩና እየደከሙ እንደሄዱ የሚናገሩ ወገኖች ቁጥራቸው ጥቂት የሚባል አልሆነም። የድህነት መንሰራፋትም ሌላው ራስ ምታት ነው።

አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን ችግሮችን ተቋቁሞ ለማለፍ ብርታት ከሚያጥራቸው እንዲሁም ለብዙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች የበለጠ ተጋላጭ ከሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ይመደባሉ። ብዙ ደክመው በማምሻ እድሜያቸው ላይ አቅም የከዳቸው አረጋውያን፣ የቤተሰብና የዘመድ እንክብካቤ በሚፈልጉበት የእድሜያቸው ምዕራፍ ላይ ለችግር ተጋላጭ ሲሆኑ ችግሮችን የሚቋቋሙበት ብርታት አያገኙም። አዕምሮ የሰውነት ሞተር ነውና በተለያዩ ምክንያቶች ለአዕምሮ ሕመም የተዳረጉ ዜጎች የሚያጋጥማቸው የሕይወት ፈተናም በቃላት የሚገለፅ አይደለም።

የበጎ አድራጎት ተግባራት እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል በዋጋ የማይተመን ሚና አላቸው። ድህነትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለተንሰራፋባቸው ማኅበረሰቦች፣ የበጎ አድራጎት ተግባራት የማኅበራዊ ፈውስ ሁነኛ መገለጫዎችና መሳሪያዎች ሆነው ያገለግላሉ። የበጎ አድራጎት ተግባራት ገንዘብን፣ ፍቅርን፣ ጊዜንና ሌሎች ሀብቶችን ከራስ ቀንሶ ለሌሎች በማካፈል የሌሎችን ችግር ለማቃለል፤ ፍቅርን፣ መተሳሰብንና አንድነትን ለማጠንከር እንዲሁም መተሳሰብና መከባበር የሰፈነበትን ማኅበረሰብ ለመፍጠር ተኪ የሌለው አወንታዊ ሚና አላቸው።

መረዳዳት የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነና የእርስ በእርስ ማኅበራዊ መስተጋብራቸውን አጠንክሮ የኖረ ተግባር መሆኑ ይታወቃል። መረዳዳት ባይኖር ኖሮ አሁናዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አሁን ከሚታየው የተለየ ይሆን ነበር።

ይህ መረዳዳትና መተጋገዝ በብዙ መንገዶች ይከወናል። በተናጠልና በጥቂት ግለሰቦች ስብስብ ከሚከናወኑ የመረዳዳት ተግባራት በተጨማሪ፣ መደበኛና ሕጋዊ አሰራሮችን ተከትሎ የበጎ አድራጎት ተቋማትን የማቋቋምና የመስራት ተግባርም በስፋት የሚታወቅ አሰራር ነው።

በኢትዮጵያ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ምግባረ ሰናይ ዓላማዎችን አንግበው የተቋቋሙና የሚንቀሳቀሱ በርካታ የበጎ አድራጎት ተቋማት አሉ። እነዚህ ተቋማት የተቸገሩ ወገኖች የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ በማድረግ ድጋፍ የተደረገላቸው ዜጎች የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው በማስቻል ሞራልና ማኅበራዊ ፍትሕ የሰፈነበት ማኅበረሰብና አገር ለመገንባት ቀላል የማይባል ሚና ይጫወታሉ።

በዚህ ዓይነት ምግባረ ሰናይ ተግባር ላይ ከተሰማሩ ተቋማት መካከል አንዱ ‹‹ሐበሻ የአረጋውያንና ምስኪኖች መርጃ ልማት ድርጅት›› ነው። የድርጅቱ መስራችና ስራ አስኪያጅ አቶ ዮርዳኖስ ፍቃዱ ‹‹ሐበሻ›› የአረጋውያንና ምስኪኖች መርጃ ልማት ድርጅት በዋናነት አረጋውያንን፣ የአዕምሮ ሕሙማንንና የጎዳና ተዳዳሪዎችን በመርዳት ተግባር ላይ ተሰማርቶ እንደሚገኝ ይገልፃሉ። ድርጅቱ የተመሰረተው በሚያዝያ 2008 ዓ.ም ነው። ድርጅቱ በደብረ ብርሃን ከተማ በሚገኘው ማዕከሉ እንዲሁም ከማዕከሉ ውጭ በሚያከናውናቸው ተግባራት ለአረጋውያን፣ ለአእምሮ ሕሙማን፣ ለጎዳና ተዳዳሪዎችና አቅም ለሌላቸው ወገኖች ልዩ ልዩ ድጋፎችን ያደርጋል።

‹‹ማኅበሩን ለመመስረት መነሻ የሆኑ ብዙ ምክንያቶች አሉ። በተለይ ደብረ ብርሃን አካባቢ አየሩ በጣም ቀዝቃዛ ስለሆነ፣ ሰዎች ጎዳና ላይ ወድቀው በሚያድሩበት ጊዜ ጠዋት በሕይወት ላይገኙ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም በቅዝቃዜው ምክንያት ከፍተኛ የነርቭና የአካል ጉዳት ያጋጥማቸዋል። ›› ሲሉ ስራ አስኪያጁ ይገልጻሉ።

‹‹ በሌላ በኩል በሰሜን ሸዋ ብዙ ገዳማት አሉ። አንዳንድ ሰዎች ታማሚ ሰዎችን ይዘው ወደ ገዳማት ሄደው፣ ከህመማቸው ካልዳኑላቸው እዚያው ገዳማት ትተዋቸው ይሄዳሉ። እነዚህ ሰዎች ወደ ደብረ ብርሃን መጥተው የጎዳና ተዳዳሪ ሲሆኑ ይታያል። አንዳንዶቹ ገንዘብ ሲያገኙ የሚበላ ነገር ገዝተው ሊበሉ ይችላሉ፤የአካል ጉዳት ያለባቸው ደግሞ ገንዘብ ቢያገኙም መጠቀም አይችሉም። ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ የሀገሪቱ ከተሞች ላይ ብዙ የበጎ አድራጎት ተቋማት የሉም፤የኅብረተሰቡ አመለካከት ጥልቅ ስላልሆነ ብዙ ድጋፍ የሚያደርግ የለም››በማለትም ያብራራሉ።

እንዲህ ዓይነት ተቋማት ስለሌሉ ሰዎች ይጎዳሉ። ደብረ ብርሃን ላይ እንኳ የሚደግፉቸውና የሚረዳቸው አጥተው ጎዳና ላይ ለመውጣትና ለመለመን ጫፍ ላይ የደረሱ በርካታ ሰዎች አሉ ሲሉ ገልጸው፣ ድርጅቱ የተመሰረተው እነዚህን አሳዛኝ እውነታዎች መነሻ በማድረግ መሆኑን አቶ ዮርዳኖስ ስለድርጅት አመሰራረት ያስታውሳሉ።

አቶ ዮርዳኖስ እንደሚሉት፣ ድርጅቱ ስራውን የጀመረው ሁለት እናቶችንና ሦስት አባቶችን ከወደቁበት በማንሳት ነው። ድርጅቱ የሰው ልጅ በሕይወት ለመቆየት የሚስፈልጉትን መሰረታዊ ነገሮችን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ ድጋፎችን ያደርጋል። የምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳት፣ ህክምና፣ ትምህርትና ሌሎች እገዛዎችን የሚያደርግ ሲሆን፣ ድጋፍ የሚሰጠውም በተለያዩ መንገዶች ነው። ከድርጅቱ የድጋፍ ማቅረቢያ መንገዶች አንዱ በማዕከሉ ለሚኖሩ ወገኖች የሚደረገው ድጋፍ ነው። በአሁኑ ወቅት በድርጅቱ ማዕከል ውስጥ 300 አረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን ቋሚ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል። ከማዕከሉ ውጭ የሚደረገው ድጋፍ በሁለት ዓይነት መልኮች (የቤት ለቤት ድጋፍ የሚደረግላቸው እና የምግብ፣ የአልባሳትና የንፅህና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ማዕከሉ የሚመጡ) ይከናወናል።

በማዕከሉ የሚኖሩ ሰዎች የእደ ጥበብ ስራዎችን ይሰራሉ፤የጓሮ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን ያመርታሉ። አልፎ አልፎ በጎችን ያደልባሉ። ከዚህ በተጨማሪም በሙከራ ደረጃ እየተሰሩ ያሉ ሌሎች ስራዎች መኖራቸውን የሚገልፁት አቶ ዮርዳኖስ፣ ‹‹ማዕከሉ በሚደረግለት ድጋፍ ውስንነት ምክንያት ብዙ ነገር ቢጎድለውም ባለው አቅም ድጋፍ ለሚያደርግላቸው ዜጎች ከምግብ፣ አልባሳትና መጠለያ በተጨማሪ ስራ እንዲለምዱና እንዲሰሩ እደረገ ይገኛል›› በማለት ይናገራሉ።

በዚህም በአሁኑ ወቅት 80 ሰዎች የቤት ለቤት ድጋፍ እየተደረገላቸው ሲሆን፣ ተፈናቃዮችን ጨምሮ ወደ ማዕከሉ በመምጣት አገልግሎት የሚያገኙ (ተመላላሽ ተረጂዎች) ደግሞ ከ600 በላይ ናቸው። በአጠቃላይ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺ በላይ ወገኖችን በመደገፍ ላይ ይገኛል። ስራ ከጀመረ ጊዜ አንስቶም /ባለፉት ስምንት ዓመታት/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከ15ሺ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል። ድርጅቱ ሰዎች በሕይወት ሳሉ ከሚያደርግላቸው ድጋፍ ባሻገር፣ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩም እንደየሃይማኖታቸው ከሌላው ሰው እኩል ስርዓተ ቀብራቸውን ያስፈፅማል።

‹‹ሐበሻ›› የአረጋውያንና ምስኪኖች መርጃ ልማት ድርጅት የበጎ አድራጎት ማኅበር ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ባከናወናቸውና ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ባሏቸው ማህበረሰብ ተኮር ተግባራት በጉስቁልና ውስጥ የነበሩ የበርካታ ሰዎች ሕይወት በበጎ ተለውጧል። ድርጅቱ ባደረገላቸው ድጋፍ ብዙዎች ሕይወታቸው ተለውጦ በጥሩ የኑሮ ጎዳና ላይ ይገኛሉ። ፈፅሞ ራሳቸውን የማያውቁ የነበሩ (መንቀሳቀስ፣ መመገብና መፀዳዳት የማይችሉ) ሰዎች በድርጅቱ ድጋፍ ተደርጎላቸው ከማዕከሉ ወጥተው እንደፍላጎታቸው የራሳቸውን ሕይወት ወደ መምራት የገቡበት (ትዳርም የያዙ፣ ትምህርታቸውን የተማሩ…፣ ሁኔታም እንዳለም ጠቅሰው፤ በማዕከሉ ውስጥም እያገለገሉና በወሳኝ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ ያሉ ግለሰቦችም እንዳሉ ጠቅሰዋል። ‹‹ብዙ ስኬታማ ወጣቶችና የስኬት ታሪኮች አሉ›› በማለት አቶ ዮርዳኖስ ስለድርጅቱ ስኬቶችና ውጤቶች ጠቅሰዋል።

ድርጅቱ በቦርድ የሚመራና የሚተዳደር ሲሆን፣ የበጎ አድራጎት ስራዎቹን ለማከናወን የሚያስፈልገውን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያገኘው የድርጅቱን ስራ እየተመለከቱ ድጋፍ ከሚያደርጉ በጎ ፈቃደኞች (የቴሌ፣ የውሃ ልማትና ሌሎች ተቋማት ሰራተኞች፣ ግለሰቦች…) ነው።

ድርጅቱ ስራዎቹን ሲያከናውን ስለሚያጋጥሙት ችግሮችም አቶ ዮርዳኖስ ሲያብራሩ፤ ‹‹በስራው ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ውጣ ውረዶች ችግር ወይም ፈተና ብቻ ተብለው የሚገለፁ አይደሉም። እንኳንስ ይህን ያህል ሰፊ የበጎ አድራት ስራ እየሰሩ፣ በቤተሰባዊ ሕይወት ላይም ብዙ ችግሮች ያጋጥማሉ። በበጎ አድራጎት ስራው ሂደት የሚያበሳጩ፣ ተስፋ የሚያስቆርጡና የሚያስተክዙ ብዙ አጋጣሚዎች አሉ›› በማለት ተናግረዋል።

‹‹ማኅበረሰቡን ለማሳመን ማኅበረሰቡን የሚመራው አካል በቅንነት የበጎ ስራው ባለቤት ካልሆነ፣ ከባድ ፈተና ያጋጥማል። ከመተባበር ይልቅ ዙሪያውን ያሉ አካላት በተቃራኒ መስመር ሲቆሙ ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል። ክልል ላይ እንዲህ ዓይነት የበጎ አድራጎት ተቋማት በብዛት የሌሉት እንዲህ ዓይነት ፈተናዎች ስለሚበዙ ነው›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ኅብረተሰቡም ሆነ አመራሩ ስለበጎ አድራጎት ያለው ግንዛቤ አነስተኛ እንደነበር አስታውቀዋል።

ልምዱንና ግንዛቤውን ለማሳደግ በብዙ ፈተና እንደደረሰባቸውም ገልጸዋል። የገንዘብና የቁሳቁስ እጥረትም ሌላው ፈተና መሆኑን አመልክተው፣ በሀገሪቱ የተከሰቱ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች በድርጅቱ ስራ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና እየፈጠሩ እንደሚገኙና ድርጅቱ የሁሉንም ዜጎች ድጋፍ እንደሚሻም አቶ ዮርዳኖስ በአፅንዖት አስገንዝበዋል።

የመንግሥት አካላትን ድጋፍ በተመለከተም፣ ከዚህ ቀደም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ስራው ይመለከተናል ብለው በሚገባ ይሰሩበት እንዳልነበር አስታውሰው፣ አሁን ያሉት አመራሮች በተሻለ ሁኔታ የማዕከሉን ተግባራት የመረዳትና የመደገፍ እንዲሁም ለበጎ አድራጎት ስራዎች ቀናዒ አመለካከት እንዳላቸው አቶ ዮርዳኖስ ይገልፃሉ።

አንዳንድ ጊዜ መሰናክልም የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉም ተናግረዋል። ‹‹ጉዳዩ ‹የእኛም ጉዳይ ነው› ብሎ በባለቤትነት የመያዝ አመለካከት ግን አሁንም ገና ነው›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ‹‹ሐበሻ›› የአረጋውያንና ምስኪኖች መርጃ ልማት ድርጅት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ያሏቸው ማኅበረሰብ ተኮር ተግባራትን ሲያከናውን በመቆየቱ ከደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር እውቅና እንደተቸረውም አስታውቀዋል።

ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እነዚህ ወገኖች ከችግሮቻቸው ተላቅቀው በማኅበረሰብና ሀገር ግንባታ ሂደት የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ የማድረግ ዓላማን ይዞ የሚንቀሳቀሰው ‹‹ሐበሻ›› የአረጋውያንና ምስኪኖች መርጃ ልማት ድርጅት እለታዊ ድጋፎችን ከማድረግ የተሻገረ የረጅም ጊዜ እቅድ እንዳለውም ስራ አስኪያጁ አቶ ዮርዳኖስ ይገልፃሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ድርጅቱ ከብትና በግ የማድለብ፣ የንፅህና መጠበቂዎችን የማምረት፣ የእደ ጥበብ ስራዎችን የማስፋፋት፣ ንብ የማነብ፣ አትክልትና ፍራፍሬ የማልማት ተግባራትን በስፋት በማከናወን፣ ከአምስት እስከ አስር ዓመታት ባለው ጊዜው ከልመና የፀዳ፣ የሰው እጅ ከመጠበቅ የነፃ፣ ራሱን የቻለና ራሱን የሚያስተዳድር የበጎ አድራጎት ድርጅት የመሆን እቅድ አለው።

ስራ የሌላቸው ሰዎች ወደ ማዕከሉ ገብተው ሰልጥነው የስራ እድል የሚያገኙበትን እድል የመፍጠር ዓላማም አለው። በአጠቃላይ ድርጅቱ ከሰው የሚጠብቅ ሳይሆን ሌሎችን መደገፍ የሚችል አቅም እንዲኖረው የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን የማከናወን ትልቅ ግብ አስቀምጦ በመስራት ላይ ይገኛል። የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት በመሆኑ ለእቅዱ መሳካትም ድርጅቱ የዜጎችና የባለድርሻ አካላትን ሁለንተናዊ ድጋፍ እንደሚፈልግ አቶ ዮርዳኖስ ይገልፃሉ።

> **በዚህም በአሁኑ ወቅት 80 ሰዎች የቤት ለቤት ድጋፍ እየተደረገላቸው ሲሆን፣ ተፈናቃዮችን ጨምሮ ወደ ማዕከሉ በመምጣት አገልግሎት የሚያገኙ (ተመላላሽ ተረጂዎች) ደግሞ ከ600 በላይ ናቸው። በአጠቃላይ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺ በላይ ወገኖችን በመደገፍ ላይ ይገኛል። ስራ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ፣ ባለፉት ስምንት ዓመታት ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከ15ሺ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል**

# በግድቡ ግንባታ የታየው አንድነት በባሕር በር ጥያቄአችንም ሊደገም ይገባል!

**ታሪኩ ዘለቀ**

በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ‹‹ቀይ ባሕር እና አባይ ኢትዮጵያን የሚበይኑ፣ ከኢትዮጵያ የተቆራኙ፣ ለኢትዮጵያ እድገትና ጥፋት መሰረት ናቸው›› ብለው ነበር። እርግጥ ነው በዘመነው የዓለማችን መልከአ ፖለቲካ ውሀ ከመጠጥነት የተሻገረ የሉአላዊነት ዘብ፣ የሀገር እድገትም መሰረት ነው።

ኢትዮጵያም በውሀ መስመሮች ላይ ጥቅሙን ባሰላው የዘመናችን መልከአ ፖለቲካ ለመጠቀም ከዓመታት በፊት በጉባ ትልቅ ሕልም ሰንቃ፣ ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ መሰረት ጥላለች ። የጨለመ ሕይወት፣ የደበዘዘ ቤት፣ ኑሯቸው ፈተና የሆነባቸው ሚሊዮን ልቦች እንደ አንድ የሆኑባት ወርቃማ እለት፤ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም። በዚች እለት በጉባ ሰማይ ስር የተቋጠረ የኢትዮጵያውያን ሁሉ የነፍስ ሕልውና የሆነ የሀገር ትርክትን ቀያሪ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ምድር እውን ሊሆን ተስፋ ተቋጥሮ፤ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ጅማሮ እውን ሆነ።

የጅማሮው መጀመሪያ የፕሮጀክቱ የሲቪል ግንባታ ስምምነት ፊርማ ነበር። የወቅቱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና የጣሊያኑ ሳሊኒ ደግሞ ተዋዋዮቹ አካላት ናቸው። ሁለተኛና ሶስተኛ ስምምነቶችም በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ቡድን መካከል ጥቅምት እና ህዳር 2004 ዓም ተፈረሙ። ከዚህ በኋላ ሳሊኒ ግንባታውን፣ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራውን ሊከውን በጉባ ተራሮች ስር ከተሙ።

ወንዝን ተንተርሰው የጨለመባቸው፣ ውሃን ተመርኩዘው ውሀን የተጠሙ ኢትዮጵያውያንም ለዚህ ፕሮጀክት ስኬት በአንድ አበሩ፤ በሕብረትም ተሰለፉ። ኢትዮጵያውያን ይህንን ታላቅ ፕሮጀክት ሲጀምሩ መነሻቸው ቁጭት፣ መድረሻቸው ጭለማን በብርሀን መተካት ነበር። ለዚህም 13 የትጋት ዓመታት ከ4 ሺህ 748 በላይ የተስፋና የግንባታ ቀናትን ቆጥረዋል። አስደማሚ የግንባታ ፍጥነት የአባይን የውሀ ፍሰት ቅየራ፣ ተደጋጋሚ የውሀ ሙሌት፣ ፈታኝ የግንባታ ምዕራፎች በእነዚህ ዓመታት አልፈዋል።

በዚያው ልክ ፍጥነቱን በገቱ፣ ጊዜውን ባጓተቱ የግንባታ ምዕራፎችም ተፈትኗል። በብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ተይዘው የነበሩት የኤሌክትሮ ሜካኒካል እና የብረት ገጠማ ስራዎች በጥራትና በፍጥነት ከደረጃቸው ዝቅ ማለትም ከፈተናዎቹ የሚመዘዙ ናቸው። በግንባታ ፕሮጀክቱ የተስተዋሉ የአስተዳደርና የብልሹ አሰራር እንከኖች በተጨማሪ በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

ከፈተናዎች ውስጥ ነጥሎ የግድቡን ሕልውና በመታደግ ደረጃ በለውጡ መንግስት የተወሰዱ ጥናት ላይ የተመረኮዙ አሰራሮችና ውሳኔዎች አበርክቷቸው ከፍ ብሎም ይነሳል። ያለፉት ስድስት ዓመታትም የግድቡ ትንሳኤ ተብለው የሚጠቀሱትም በዚሁ ምክንያት ነው። የወቅቱ ፈተና ታሪካዊ ሁነት እውን ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ‹‹የዛሬ አምስት ዓመት እዚህ ቦታ ስንመጣ ይሄ ግድብ ውሀ አልነበረውም። ይሄ ግድብ ይህ ግርማ ሞገስ አልነበረውም። ይሄን ግድብ ከችግሩ አውጥተን እናርቀው፣ እናርመው ሲባል ፈተናውም ቀላል አልነበረም። ያን ጊዜ የነበረውን ፈተና የምናውቅ እናውቃለን፤ የሌሉ ሰዎች ላይገባቸው ይችላል›› ብለዋል።

በዚህ ሁሉ ሂደት ግን የግድቡን ግንባታ ለማጓተት ቢቻልም ለማስቀረት የሚደረጉ ተፅዕኖዎች ቀላል አልነበሩም። ከካርቱም እስከ ግብፅ ደግሞም እስከ ተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት የዘለቁ ውንጀላዎች ከእነዚህ ይመነዘራሉ። የውስጥ ፈተናዎችም የግድቡ ግንባታ መሰናክሎች ነበሩ። በፈተናዎች ውስጥ የፀናው የግድቡ ግንባታ ሐምሌ 2013 ዓ.ም በግድቡ ሁለት የሀይል ማመንጫ ተርባይኖችን ማንቀሳቀስ የሚያስችል ውሀ መያዝ የቻለበት ሁለተኛ ዙር የውሀ ሙሌት ተከናወነ። በኢትዮጵያ በኩል ከተፋሰሱ ተጋሪ ሀገራት ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ጥረቱን የቀጠለው ግንባታው በነሐሴ ወር 2014 ዓ.ም የግድቡን ግራና ቀኝ ከፍታ 611 ሜትር ላይ አድርሶ ውሀው በግድቡ አናት ላይ መፍሰስ መጀመሩ ተበሰረ።

በዚህ ሶስተኛው ዙር የተያዘው የውሀ መጠን 22 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር እንዲደርስም አድርጎታል። ባለፈው ዓመት አራተኛ ዙር የውሀ ሙሌትም ተከናውኗል። ከሰሞኑም ግድቡ ሌላ የስኬት ምዕራፍ የግድቡ ሶስተኛና አራተኛ ተርባይነሮች ስራ ጀምረዋል። ወደ ታችኛው የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት ተጨማሪ የውሀ ማስተንፈሻ በሮችም ተከፍተዋል። ታላቁ ሕዳሴ ግድብ የሲቪል ስራው እስከ መጪው ታህሳስ ወር ድረስ ይጠናቀቃል። ኢትዮጵያውያን በአንድነት ገንዘባቸውን፣ ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ የሰጡበት፣ ምኞት ተስፋቸውን የጣሉበት፣ ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን መሀንዲስ፣ የፋይናንስ ምንጭም ሆነው የገነቡት ግድብ ነው።

ታላቁ የሕዳሴ ግድብ እንደ ዓባይ ገባሮች በሕብራዊነት የተዋሀደ፣ በሕዝቦች አንድነት ከጉባ ተራራ ስር እውን የሆነ ነው። ታላቁ የሕዳሴ ግድባችን እራትም ብርሀንም የሆነ የእኛ የኢትዮጵያዊያን ግድብ ነው። ዓባይ ለዘመናት የረባ ጥቅም ሳይሰጥ ወደ ጎረቤት ሀገራት ሲሰደድ የሚታይ እንጂ የማይበላ እንጀራ ሆኖ መቆየቱንም እንደትዝታ የምንዘክርበት፣ የታሪክ ምዕራፎች የተዘጉበት እውነት ላይ ደርሰናል። በበርካታ ውጣውረዶች ውስጥ ያለፈው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ከባድ የሚመስሉ የዲፕሎማሲ ጫናዎችን ተሻግሮ አሁን ላይ ወደ ፍፃሜው እየተንደረደረ ይገኛል።

ምንም እንኳ የታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት የግድቡን መገንባት ተከትሎ ድርቅ ሊከሰት ይችላል፣ የአስዋን ግድብ ይቀንሳል የሚሉ ክሶችን ሲያቀርቡ ቢደመጡም አሁንም ግን ኢትዮጵያ የጎርፍ አደጋ ስጋትን በመቀነስ ለታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በተለይ በድርቅ ዘመን መጠኑ ያልዋዠቀ የውሀ አቅርቦት እንዲደርሳቸው እያደረገች ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንዳሉትም፤ ኢትዮጵያ ብቻዋን ለመጠቀም ምን አይነት ፍላጎት የላትም። ኢትዮጵያውያን ተካፍሎ መብላት የሚወዱ ሕዝቦች ናቸው። እንደ ሀገርም ኢትዮጵያ ማንንም የሚጎዳ የዲፕሎማሲ መንገድ ተከትላ አታውቅም። በታሪኳ ያስተናገደቻቸው መሪዎችም ከጎረቤት ሀገራት ጋር ትብብር የሚሹ እንጂ ተቃርኗዊ ዲፕሎማሲ ተከትለው አያውቁም።

ኢትዮጵያ በርካታ ውስጣዊ እና ውጫዊ ጫና ቢኖርባትም በሕዳሴ ግድብ ላይ የምታከናውነውን ስራ ለሰከንድ ሳታቋርጥ ዛሬ ላይ ደርሳለች። ኢትዮጵያ በሕዳሴው ግድብ ጉዳይ የዕውነት፣ የዕውቀትና የፍትሀዊነት መርህን ይዛ በትብብር መንገዶችም ውጤታማ ሆናለች። ከጉባ እስከ ፀጥታው ምክር ቤት የደረሰ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ አጀንዳ ከሰሞኑ ብስራትን አሰምቶናል።

የታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት የሆኑት ግብፅና ሱዳን አሳሪ ስምምነት ሳይፈረም ኢትዮጵያ ግድቡን ውሃ እንዳትሞላና ስራ እንዳትጀምር ሲፈጥሩት የነበረውን ጫና ተሻግሮ ተጨማሪ የኃይል ማመንጨት ደረጃ ላይ ይገኛል። ሕልምም እውን ሆኗል። ከሊቅ እስከ ደቂቅ ዋጋ የከፈሉበት የሕዳሴ ግድባችን የሚጨበጥ ተስፋ ሆኖ የሕዝቦች ኩራትም እየሆነ ይገኛል።

ያለፈውንም ሆነ መፃኢ ጊዜዋን የውሀ አካላት የሚወስኑላት ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ድልም በዓለም መድረክ ገናናነቷን ለመመለስ መስፈንጠሪያዋ ነው። የዲፕሎማሲ ጫናናን ተቋቁማ የአፍሪካ ችግሮችን አፍሪካዊ መፍትሄ እንደሚሰጥ ትምህርትን ለተቀረው ዓለም አስተምራለች። የፕሮጀክቱ ሂደት ጥቅል ስኬቱ ግን የሕዝብ አብሮነት በፈተና ውስጥ መፅናት፣ የአቅምና የዕውቀት ትብብር የማያሳካው እንደማይኖር በጉባ ሰማይ ስር አስመስክሯል። ሕዝቦቿም ከመንግስት ጋር እጅና ጓንት ሆነው የልማት ጦርነትን እንዴት እንደሚያንኮታኩቱ በጉባ አሳይተዋል ማለት ይቻላል።

> **የሕዳሴ ግድብ ድልም በዓለም መድረክ ገናናነቷን ለመመለስ መስፈንጠሪያዋ ነው። የዲፕሎማሲ ጫናናን ተቋቁማ የአፍሪካ ችግሮችን አፍሪካዊ መፍትሄ እንደሚሰጥ ትምህርትን ለተቀረው ዓለም አስተምራለች**

ለመጠናቀቅ ጫፍ የደረሰው ግድባችን አሁንም የሕዝቡን ተሳትፎ ይሻል። አንድም በደለል እንዳይጠቃ ችግኞችን በብዛት መትከል ሁለትም ሕዝባዊ ድጋፍ ማሰባሰቢያዎች ላይ በንቃት በመሳተፍ የምርቃት ሪባኑ እስከሚቆረጥ በሕብረት መቆም ይጠበቃል። የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ዛሬ ከማይቀለበስበት ምዕራፍ ቢደርስም ሂደቱ ግን አልጋ በአልጋ አልነበረም። ብዙ የተለፋበት፣ ኢትዮጵያውያን በጋራ ሆነው በጉልበትም፣ በገንዘብም የተሳተፉበት፣ በበርካታ ውጣ ውረድ ውስጥ ያለፈ ፕሮጀክት ነው። ኢትዮጵያውያን ለሀገራቸው ልማትና ብልፅግና ወደኋላ እንደማይሉ በተግባር ያሳዩበት ፕሮጀክት ነው።

ታዲያ በዚህ ፕሮጀክት ላይ የተስተዋለው የኢትዮጵያውያን አብሮነት በዛሬው የሕልውና ጥያቄአችን የባሕር በር ላይ ሊደገም ይገባል። የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ ለኢትዮጵያ የአማራጭ ጉዳይ አይደለም። እንደ ከዚህ በፊቱ መቀጠል አንችልም። የብሔራዊ ጥቅም፣ የመኖር አለመኖር የሕልውና ጉዳይ ነው። ይህንን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገንዝቦ ሕዳሴ ግድብ ላይ እንደ ኢትዮጵያዊ ያሳየነውን መተባበር እና ድል የባሕር በር ለማግኘት በሚደረገው ጥረት ላይም ሊደግመው ይገባል።

ኢትዮጵያ ጠላቶቿ እንድትተራመስ ቢወጥኑም፣ በዓለም አቀፍ ተቋማት ተፅእኖ እንዲደረግባት ግፊት ቢያደርጉ ስለ አባይና ስለምታገኘው የባሕር በር ብቻ አይደለም፤ በአጠቃላይ ሀገሪቱ በአፍሪካ ቀንድ ብሎም በዓለም አቀፍ የውሀ መስመሮች ላይ ስለምትፈጥረው አቅም እንጂ። ለዚህም ነው ትላንት የሕዳሴ ግድቡን ግንባታ ለማሰናከል የተነጣጠሩ የሴራ ወንጭፎች ዛሬም በባሕር በር ጥያቄዎች ላይ በድጋሚ የሚወረወሩት።

እነዚህን ሴራዎች አክሽፎ ለማለፍ በሕዳሴው ግድብ ላይ የነበረን አንድነት በባሕር በር ጥያቄአችን ላይም ተጠናክሮ ሊደገም ይገባል። ዓባይ ላይ እንደተባበርን ሁሉ በባሕር በር ጉዳያችን ላይም በዛው ልክ መተባበር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ በሁለትና በሶስት በኩል የባሕር በር ማግኘቷ ሀገራችን ላይ የሚያመጣውን ጥቅም መገንዘብ ያስፈልጋል። የንግድ ሁኔታችን ይጨምራል፣ የኢኮኖሚ ሁኔታችን ያድጋል፣ ደህንነታችን የተረጋገጠ ይሆናል፣ የፖለቲካ ችግሮቻችንም በዛው ልክ እየተቀረፉ ይሄዳሉ።

ኢትዮጵያ በበርካታ ችግሮች ውስጥ እያለፈችም ቢሆን የሕዳሴ ግድብ ግንባታ አሁን ባለበት ደረጃ ማድረሷ ትልቅ ስኬት ነው። የአሁኑ ትውልድ የአንድነት ማሰሪያና የጋራ ቋንቋም የባሕር በር ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ ትላንት በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ጥንስስ ጅማሮ እንደሆነው ሁሉ የዛሬውም የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ምንም እንከን ሳይገጥመው የሚሳካ አይደለምና የጠነከረ አቋም፣ ሕዝባዊ አንድነትና የበሰለ የድርድር ስራን የሚፈልግ ነው። ይህ ደግሞ የመንግስትንና የሕዝብን ጣምራ ስራን ይፈልጋል።

በእርግጥ ዛሬ ላይ ከብዙ አንድ ከሚያደርጉን ነገሮች ይልቅ የሚለያዩንን ጥቂት ነገሮች ለማጉላት የሚሞክሩ አይጠፉም። ግን ደግሞ እንደ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ያሉ ስራዎች የአብሮነታችን ውጤቶች ናቸው። ይህን ስኬት በባሕር በር ባለቤትነት ለማስቀጠልም የኢትዮጵያውያን አንድነትና በጋራ መቆም፣ መተባበርና መደማመጥ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው። ለውጭ ጠላቶች የኢትዮጵያን ብልፅግና ማጨናገፊያ መንገዶች የሀገር ውስጥ አለመግባባቶች እንደመሆናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን በአግባቡ ተረድቶ አንድነቱን ይበልጥ ሊያጠናክር ይገባል!

# ስፖርት





# ‹‹መመሪያውን የወሰነው አካል በአግባቡ መፈጸም ይኖርበታል››

### -አቶ ክፍሌ ሰይፈ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ስራ አስኪያጅ

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክሲዮን ማህበር የክለቦች የክፍያ ስርዓት አስተዳደር መመሪያን አውጥቶ ለማስፈጸም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። መመሪያው እንዲወጣ ምክንያት የሆነው የክለቦች የዝውውርና ክፍያ ስርዓቱ ግልፅ ያልሆነና ብዙ ማጭበርበሮች ያሉበት መሆኑን ተከትሎ እንደሆነ የአክሲዮን ማህበሩ ስራ አስኪያጅ አቶ ክፍሌ ሰይፈ ያስታውሳሉ፡፡

የክለቦች የክፍያ ስርዓት አስተዳደር መመሪያ ወደ ትግባራ ከገባ በኋላ ለማስፈጸም ገለልተኛ ኮሚቴ ተቋቁሞ ለተግባራዊነቱ እየሰራ ነው። ይሁን እንጂ ከተጫዋቾች ዝውውርና ከክፍያ ስርዓቱ ጋር ተያይዞ አሁንም መመሪያው እየተከበረ እንደማይገኝ ቅሬታዎች ይሰማሉ። ተጫዋቾች በዝውውር መስኮቱ አንዱ ክለብ ያቀረበላቸውን የተሻለ ክፍያ በመተው ትንሽ ክፍያ ላቀረበ ክለብ ሲፈርሙ መታየታቸው ደግሞ በመመሪያው ተግባራዊነት ላይ ጥርጣሬን ያሳደረ አንዱ ምክንያት ነው።

መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ክፍሌ፣ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ተጫዋቾች የክፍያ ስርዓት ግልጽ ያልሆነ ማጭበርበር የሚበዛበት በመሆኑ ከክለቦች በመጣ ጥያቄ መሰረት ጥናት ተደርጎ አዲስ መመሪያ ወደ ትግበራ መግባቱን ያስታውሳሉ። መመሪያውን የሚያስፈጽመው አካል ገለልተኛ መሆን ስለሚኖርበት ከተለያዩ ክፍሎች



**አቶ ክፍሌ ሰይፈ፣**

የተወጣጡ ሰዎችን ያቀፈ አጣሪ ኮሚቴ ከእግር ኳስ ፌዴሬሽን ዲሲፕሊን ኮሚቴ፣ ከስነ-ምግባርና ፀረሙስና፣ ከፌደራል ፖሊስ፣ ከደህንነት እና ከጠበቆች ማህበር ተዋቅሮ ስራ መጀመሩን ይጠቁማሉ። ኮሚቴው ደንብና መመሪያውን በማንበብ እራሱ የሚመራበትን የስነ ምግባር መመሪያንም ደንብ ማዘጋጀትም ተችሏል፡፡

ኮሚቴው የተጫዋቾች ዝውውር በክለቦች ምን እንደሚመስል ከ19ኙም ክለቦች መረጃ እንዲሰበሰብ ጠይቆ መረጃዎች ለጽህፈት ቤቱ እየደረሱ መሆናቸውንም ስራ አስኪያጅ ይናገራሉ። እየቀረቡ በሚገኙ መረጃዎች መሰረት አንድ ተጫዋች ከአንድ ክለብ ጋር የተነጋገረውን ከፍተኛ የደመወዝ ክፍያ በመቀነስ ለሌላ ክለብ በፌዴሬሽን ውል ላይ የ150 ሺ ብር ልዩነት ያላቸው ውሎችን ሲፈፅም እየታየ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ ክፍሌ፣ ተጫዋቾችን ለማስፈረም ውል ከፈፀሙ ክለቦች ጋር መረጃ በስልክ፣ በኢሜል፣ በአካልና በሌሎች መንገዶች ጥቆማ እንዲሰጥ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በቅርቡ ይፋ በሆነው የጥቆማ ስርዓት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከዚህ ጋር የተገናኙ መረጃዎችን ማቀበል ይችላል። በዚህም ጠቋሚው አካል ከፍተኛ የሆነ ገንዘብን የሚያገኝበት ይሆናል። ለጠቋሚው የሚሰጠው መጠን ከተጭበረበረው ገንዘብ ላይ 50 ፐርሰንቱ እንደሚሰጥ ስራ አስኪያጁ ጠቁመዋል። በቦርድ ከፀደቀ በኋላ ለኅብረተሰቡ ይፋ ሆኖ በሚመጣው የጥቆማ ስርዓት መሰረት አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ እርምጃ ይወሰዳል። ክለቦች ውል እንዴት አዋዋሉ የሚለው አጣሪ ኮሚቴው ሂሳብ መዝገባቸውን በመመርመር እና በተለያዩ ስልቶች በማጣራት ላይ ሲሆን ሕገ ወጥ ድርጊት ፈጽሞ የሚገኝ ክለብ በመመሪያና በደንቡ መሰረት ውሳኔ ይተላለፍበታል።

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ አክስዮን ማህበር መመሪያውን የወሰኑ ክለቦችና አካላት በአግባቡ መፈጸም እንዳለባቸው የሚናገሩት አቶ ክፍሌ፣ ከ16ቱ ክለቦች መመሪያውን ጥሰዋል ተብለው ጥቆማ የተጠቆመባቸው ሶስት ክለቦች ላይ እንደሆነ ጠቁመዋል። መመሪያውን ጥሰው የተገኙ ክለቦች ዋንጫ ቢያነሱ እንኳን በምርመራ ከተረጋገጠ ጊዜው ቢያልፍም ዋንጫውን ተቀምተው ከሊጉ እስከ መውረድ ድረስ ቅጣት ሊተላለፍባቸው ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ሁሉም በተስማማው መጠን ሰላማዊ የእግር ኳስ መድረክ እንዲኖር የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ጥሪ አቅርበዋል። ክለቦች ሁልጊዜ ተስማምተው የሚያወጡትን ደንቦች መመርያዎች በአግባቡ መፈጸም እንዳለባቸውም ገልጸዋል፡፡

መመሪያው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ወጣቶች ቦታ እንዲያገኙ ይጋብዛል የሚሉት አቶ ክፍሌ፣ አዲስ እንደመሆኑ ግን የመንገጫገጭ ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስጋታቸውን ቢገልፁም አሁን ጥሩ ደረጃ ላይ እንዳለ ይናገራሉ። ክለቦች የራሳቸው መለያ ኖራቸው አትራፊ እንዲሆኑ ብዙ ስልጠናዎች መሰጠቱን የሚያስታውሱት አቶ ክፍሌ ይህንን ለመተግበር ክለቦች የተደራጁበት መንገድ ትክክል እንዳልሆነ ይጠቅሳሉ።

እንደ አቶ ክፍሌ ገለፃ፣ ክለቦች ከመንግስትና ከከተማ አስተዳደር ሙሉ ሀብት ስለሚያገኙ ሕዝባዊ እና የገበያ እቅድን መያዝ አይፈልጉም። የከተማ አስተዳደር ክለቦች ቀስበቀስ ከድጎማ ወጥተው የራሳቸውን ገቢ እንዲያመነጩና ትርፋማ እንዲሆኑ መስራት ይኖርበታል። የኢትዮጵያን እግር ኳስ ከችግር ለማላቀቅ ረጅም ጊዜ የሚያስፈልገው እና ክለቦች የ10 ዓመትና ከዛ በላይ እቅድ ይዞ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ክለቦች በዓመት ለአንድ ተጫዋች ምን ያህል እንክፈል እንጂ እንዴት ገበያ ተኮር መሆን እንዳለባቸው ግንዛቤ መያዝ አለባቸው፡፡

## ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የአፍሪካ ከተሞች ፎረም በአድዋ ሙዚየም

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

አብዛኞቹ የአፍሪካ ከተሞች የአውሮፓ ቅኝ ግዛት አሻራና አቧራ ያለባቸው ናቸው። በጥንታዊ ከተማነት ግን የኢትዮጵያ አክሱም፣ ላሊበላ ጎንደርና ሐረር ፤ በሰሜን አፍሪካ ከነበሩት ጥንታዊ ከተሞች መካከልም በጣም ዝነኛ የነበሩት አሌክሳንድርያ ፣ ቴብስ (Thebes) ፣ ካርቴጅ እና ሜምፊስ ይጠቀሳሉ። አፍሪካን ሲቲስ ድረ ገፅ እንደሚያስረዳው በዘመናችን ያሉት አብዛኞቹ ትልልቅ የአፍሪካ ከተሞች በደንብ የተመሠረቱት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አፍሪካ በቅኝ አገዛዝ ሥር ስትጥለቀለቅ ነው። ከከተሞቹ የባርያ ንግድም ማሳለጫ ነበሩ።

ብዙዎቹ ጥንታውያን የአፍሪካ ከተሞች ከ1ሺህ ዓመታት በፊት የነገሥታት፣ የግዛተ ዐፄዎችና (ኢምፓየር) የካሊፋዎች መቀመጫ ናቸው። ከፊሎቹም ከሮም ነገሥታት ዘመን የቀደሙም ነበሩ። ጥቂት ከተሞች የሀገርና የዓለም አቀፍ እምነቶች ወይም ንግድ ማዕከላት ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ከተሞች እነዚህን ነገሮች ያጣመሩ ነበሩ። እናም አንዳንዶቹ እንደ ቱኒስ /ካርቴጅ ዓይነቶቹ ለሮማውያን እንደ ቱሪዝም መዝናኛ አገልግለዋል።

በመግቢያችን ስለጥንታዊ የአፍሪካ ከተሞች ያነሳነው ሰሞኑን በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተካሄደው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ልናነሳ ሽተን ነው። በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን እና የአፍሪካ ኅብረት ዋና መቀመጫ፣ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ በአድዋ ድል መታሰቢያ ‹‹ዘላቂ የከተሞች ልማት ለአፍሪካ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ 2063 ›› በሚል መሪ ሀሳብ የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ተካሂዷል። በፎረሙ የተለያዩ የአፍሪካ ከተሞች ተሞክሮአቸውን አቅርበዋል። የፖሊሲ እና ስልታዊ መፍትሄዎች ምክክር ተካሂዷል።

ፎረሙን ሲከፍቱ ም/ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ኢትዮጵያ የፓን አፍሪካን እሳቤዎች ዕውን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየሠራች እንደምትገኝ ጠቁመው፤ አፍሪካ በከተሞች የሚያጋጥሟትን ተግዳሮት



እንደመልካም አጋጣሚ በመውሰድ ቅንጅታዊ አሠራሮችን በማጠናከር የወደፊቷን የአፍሪካ ዕድገት ለማሳለጥ ፎረሙ የጎላ ሚና እንደሚኖረው አንስተዋል። ችግሮቻችን በራሳችን አቅም ለመፍታት በቴክኖሎጂ ትስስር እና በሰው ኃይል በኩል የሚኖረንን አጠቃቀም በወንድማማችነት ተባብረንና ተጋግዘን የአፍሪካን መጻኢ ብልጽግና ማፋጠን አለብን ብለዋል።

የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው እንደተናገሩት ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የአፍሪካ ከተሞች ፎረም እንድታዘጋጅ የተመረጠችበት ዋና ምክንያት መንግሥት በአሁኑ ወቅት ለከተሞች እድገትና መስፋፋት ብሎም ለነዋሪዎቻቸው ምቹና ሳቢ እንዲሆኑ በቁርጠኝነት እየሠራ በመገኘቱ ነው። በአፍሪካ ፈጣን የከተሞች እድገት እየተስተዋለ ይገኛል ያሉት ሚኒስትሯ በዚህም በዓመት በአፍሪካ 3 ነጥብ 5 በመቶ እንዲሁም በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 4 በመቶ የከተሞች እድገት እንደሚታይ አስረድተዋል። እድገቱ የከተማና የገጠር ምጥጥንን የሚቀይር ማሳያ በመሆኑ አፍሪካ እንደ አህጉር በርካታ የከተማነት አጀንዳዎች አሏት። ከተሞች ሲስፋፉ በቂ የመሠረተ ልማት መስፋፋት እጅጉን አስፈላጊ ነው። ከተሞቻችን ለማሻገር ለዜጎች ምቹ መኖሪያ እንዲሆኑ ለማድረግ በጋራ መሥራት ያስፈልጋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ የኢትዮጵያ መንግሥት የከተሞች መስፋፋት ለኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ሙሉ አስተዋፅዖ እንዲያበረክት በሚያስችል መልኩ ከተሞችን ለመምራት የሚያስችሉ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። ከተሞችን ምቹ የመኖሪያ፣ የመንቀሳቀሻ፣ የምርታማነት አካባቢ በማድረግ የምጣኔ ሃብት ማዕከል ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የደቡብ አፍሪካ የሰፈራ ምክትል ሚኒስትር ታንዲ ማህምባህላላ፤ አፍሪካ ፈጣን የከተሞች እድገት የምታስተናግድ አህጉር ናት ይላሉ። በዚህም ወደ ከተሞች የሚደረገው የዜጎች ፍልሰት ከተሞች እራሳቸውን በመሠረተ ልማት ግንባታ ሊያበቁ እንደሚገባ አመላካች ነው። የከተማነት ምጣኔ ማደጉ የከተሞችን ሽግግር ያፋጥናል። የባህልና የእውቀት ልውውጡን በማሳለጥ ረገድም ጠቀሜታው የጎላ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ሥራ አጥነትን፣ ድህነትንና የአከባቢ መራቆትን የሚያስከትል በመሆኑ ለዜጎች መኖሪያ የሚሆኑ ምቹ ከተማዎችን ለመገንባት የተቀናጀ ሥራ ያስፈልጋል። ግብርና በማዘመንና ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚን በመገንባት በከተሞች አካባቢ ያለውን የሥራ እድል ፈጠራ ማጠናከር አስፈላጊ እንደሆነና ደቡብ አፍሪካም በዚህ ረገድ የተዋጣለት ተግባር እየሠራች መሆኑን ጠቁመዋል።

የግብፅ የቤቶች አገልግሎት ሚኒስትር አምባሳደር ሀሰን ኢልላኢቲ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደዚህ ዓይነት የተሳካ መድረክ በማዘጋጀቱ አመስግነው፤ መንግሥታቸው በከተሞች ልማት የሚደረገውን የትኛውንም ዓይነት ፕሮጀክት ለመደገፍ ዝግጁ መሆኑን ነው የገለፁት።

በተ.መ.ድ የኬንያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ግሬስ አካራ እንደተናገሩት፤ ከተሜነት በአፍሪካ ሁሉንም የኢኮኖሚ ገፅታዎች እየቀረጸ ነው። ይህ ፎረም የአፍሪካ ከተሞችን አሁናዊ ገጽታ ከማስተጋባት ባለፈ በአጀንዳ 2063 የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት ያለውን ቁርጠኝነት የሚረጋገጥበት እድል የሚሰጥ ነው። በአሁን ወቅት ከተሞች 55 በመቶ ለሚሆነው የዓለም ሕዝብ መኖሪያ ሲሆኑ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2050 ይህ ምጣኔ 68 በመቶ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። እ.አ.አ በ2019 የኬንያ የከተማ ሕዝብ ብዛት 31 ነጥብ 2 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2030 ወደ 50 በመቶ ያድጋል ተብሎ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል።

የከተሞች መስፋፋት ፈተናዎችን ለመፍታት ኬንያ የተለያዩ ኢንሼቲቮችንና ስትራቴጂዎችን በመተግበር ትልቅ እመርታ አምጥታለች የሚሉት አምባሳደሯ፤ አቅም ለሌላቸው ኬንያውያን ጥሩ መኖሪያ ቤቶች እንዲኖራቸው ለማስቻል ለተመጣጣኝ የቤቶች ግንባታ ፕሮግራም ቅድሚያ ተሰጥቷል። በፕሮግራሙ በዓመት 250 ሺህ መኖሪያ ቤቶችን ለማቅረብ እየተሠራ ነው ።

በፎረሙ የተመድ በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች፣ ዓለም ዓቀፍ የልማት ድርጅቶች፣ የአፍሪካ ከተሞች ከንቲባዎች፣ በኢትዮጵያ የተለያዩ የመንግሥት ኃላፊዎችና ሚኒስትሮች፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና ሌሎችም ተሳታፊዎች ነበሩ።